ኅዳር ፳፩ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም.

በስደት ላይ ላለው ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ጽ/ቤት

Oakland, California, USA

**ጉዳዩ:- በሰሜን አሜሪካ በቨርጅንያ ግዛት በምትገኘው የሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተፈጠረውን ችግር ይመለከታል።**

የቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይ የልጆቻቸውን እናት ከፈቱበት (ሰኔ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. ወይም June 2006) ጀምሮ ለበርካታ ዓመታት የቤተ ክርስቲያኗ ችግር ለተመልካች ሁሉ አሰልቺ፤ እምነታችንንና ባሕላችንን አስተቺና አስነቃፊ ሆኖ ያለ አንዳች መፍትሄ ሲጓተት መቆየቱ ለሁሉም የታወቀ ነው። ችግሩ ቤተ ክርስቲያኒቱን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በሀፍረት ላይ በመጣሉ፤ በዋሽንግተን ዲሲ በቨርጅንያና በሜሪላንድ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያኖች ተሰባስበው የራሳቸውን የቀድሞው ቄስ ታደሰን ወላጅ እናት በመጨመር በየሳምንቱ የሚታየው ውዝግብ በሽምግልና እንዲያልቅ ብዙ ጥረት አደረጉ። ይሁን እንጅ በቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይ በኩል ሽምግልናው ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀረ። ይልቁንም "**ከሁሉም ገለልተኛ አድርጌ በስሜ ባስመዘገብኩት ንብረት የፈለግሁትን ባደርግ ጠያቂ ሊኖርብኝ አይገባም በማለት እንዲያውም የአንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ዶላር ካሣ እፈልጋለሁ**" በማለት ሽምግልናውን ረግጠው ወደ ዓለማዊ ዳኛ ሄደው በክርስቲያኖች ላይ ግለሰቡ ክስ መሠረቱ። የቀሩትን ምእመናንና የደብሩን መዘምራን ከሙዳየ ምጽዋቱ በተገኘው ገንዘብ ወታደር ቀጥረው ከቤተ ክርስቲያን ማባረር ጀመሩ።

ማንም ግለሰብ ገለልተኛ ነኝ በማለት ታላቋን ቤተ ክርስቲያናችንን ለሥጋዊ ፍላጎት ርካታ መሳሪያ አድርጎ መጠቀም ተገቢ አለመሆኑን ጸንተው ከሚቃወሙት ምእመናን ጋራ መቃወም ተገቢ መሆኑን ተረዳን። የቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይ እየፈጸሙ ያሉትን አስነዋሪ ተግባር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት የማይቀበለው መሆኑን አስረድተን፤ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥና ውጭ በየሳምንቱ የሚደረገው ለተመልካች አሰቃቂ የሆነው ህዝባዊ ተቃውሞ እንዲቆም እሑድ የካቲት ፴ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም (Sunday March 10, 2014) የቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይን ለማውገዝ ተገደድን።

በወሰድነው ውሳኔ መሠረት ጉዳዩ በሕግ በኩል ለማለቅ በመቃረብ ላይ ሳለ፤ "ይመለከተዎታልና ዝም ብለው ሊያልፉት አይገባም" ላላቸው ሁሉ "የቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይ ገለልተኛ ነው። በሀገሩ ሕግ ተጠቀሙ። ጥርስ የሌለው አንበሳ ነኝ። አይመለከተኝም" ሲሉ የቆዩት አባ ፋኑኤል፤ በግለ ሰቡ ላይ የሚፈረድበትና ከቅስናውም የሚገለል መሆኑን ሲያዩ ፤ በገለ ሰቡ ላይ ሲናገሩት የነበረውን ገልብጠው፤ "በእኔ ሥር ነው" ብለው የሽፋን ወረቀት ለሚመለከተው ጻፉ። የጻፉትን የተመለከተ ሁሉ አባ ፋኑኤል ለቤተ ክርስቲያን ክብርና ቅድስና ከመቆም ይልቅ፤ ከግለሰቡ ጋራ ባላቸው ሥጋዊ ጥቅም የግለሰቡን በደል ለመሸፈን ያደረጉት ሙከራ፤ ችግሩ በራሳቸው ላይ እንዲነድ ከማድረግ በስተቀር፤ የግለሰቡን ጥፋት የሚጋርድ ሊሆን አልቻለም። ለሽፋን የጻፉት ተቀባይነት ሊያገኝ ቀርቶ፤ ችግሩን የበለጠ አጓነው። አቡነ ማትያስ በጥቅምት ወር ፳፻፮ ዓ.ም. አሜሪካንን በመጎብኘት ላይ ሳሉ፤ ጉዳዩ በማኅበረ ምእመናኑ ቀርቦላቸው "በአስቸኳይ ውሳኔው ይደርሳችኋል" ብለው ምእመናኑን አጽናንተው በገቡት ቃል መሠረት፤ ምእመናኑ የአቡነ ማትያስን ዉሳኔ በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ፤ አባ ፋኑዔል ግለሰቡን በስህተትህ ቀጥልበት የተባለ የሚያስመስል ጽሑፍ በ*ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ* ላይ አሳትመው በቨርጅንያ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ላይ መለጠፋቸው ተመልካቹንም ሆነ የእምነቱን ተካታይ ጥልቅ በሆነ ሀዘን ውስጥ ከተተው። ይህን የመሰለ አስነዋሪ ተግባር በቤተ መቅደስ መፈጸም ይቅርና በየመንደሩ እንዳይፈጸም ለዘመናት ስታወግዝ

የኖረችውን የቅስናችን ምንጭ የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችንን የግለሰቡን መጥፎ ድርጊትና ስህተት ደጋፊና ተባባሪ አድርገው ማቅረባቸው አሁን ባሉበት መስመር በቤተ ክርስቲያናችን እንዲቆዩ፤ ነገረ መለኮቱም ሆነ ቀኖናችን አይፈቅድላቸውም። ጽድቅን ተከትሎ በቀኖና ቤተ ክርስቲያናችን ለሚፈርድ አካል፤ አባ ፋኑኤል ሊሸፍኑት የፈለጉትን ግለሰብ ከገባበት አዘቅት ውስጥ ሊያወጡት ቀርቶ ራሳቸውን ጠልፈው መከተታቸውን በቀላሉ ሊገነዘበው ይችላል። አባ ፋኑኤል በተደራረበ ስህተታቸው ምክንያት በቀኖናችን መሰረት የተወገዙትን ግለሰብ ወደ ቅስና አገልግሎት መልሻለሁ በማለታቸው "ወእለ ሤሙ ላእሌሆሙ መገብተ ከህድያነ ንኡንኖሙ በግዘት በኩሉ መዋዕል ወበኩሉ መካን" (ሃይ አበ 101፡23) ማለትም፦ "ህዝባዊ የሆነውን ክህነታዊ ተልእኮ እንዲያካህድ በህዝበ ክርስቲያኑ ላይ አስነዋሪ ተግባር በመፈጸም ላይ ያለውን ግለሰብ የሰየመ፤ በሁሉ ቦታና ጊዜ ይወገዝ" የሚለው ቀኖናችን አውግዞ ከቤተ ክርስቲያናችን ያባርራቸዋል።

ከዚህ ቀደም በቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይ ላይ ያሳለፍነውን ውሳኔና፤ አሁን በአባ ፋኑኤል ላይ የምናቀርበውን ክስና ወቀሳ በአጸደ ነፍስ ያሉ አባቶቻችን ሊቃውንት ቢመለከቱት "አስተንፈስከኒ ፊንሐስ" (ዘኁል 25) የሚለውን እንደሚገሥልን አንጠራጠርም።

አዕማድ መስላችሁ ለምትታዩ አባቶችና፤ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት አበውና በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተጠምቃችሁ ላደጋችሁ፤ በዓለም ዙሪያ ተበትናችሁ ላላችሁ ወጎኖቻችን የምናሳስበው፤ አባ ፋኑኤል ተደጋጋሚ ጥፋት በመፈጸም ላይ ካለው ግለሰብ ጋራ በግላዊ ውለታና ጓደኝነት በመተሳሰር ቤተ ክርስቲያኒቱን ሲያተራምሱ ከኖሩ በኋላ፤ እንዲያውም ይባስ ብለው ለጽጽስና ትንሽ የቀረው ነው በማለት ግለሰቡን በክህነቱ አገልግሎት እንዲቀጥል ማድረጋቸው በታደሰ ሲሳይ ላይ ከተወሰደው ውሳኔ ይልቅ፤ በአቡነ ፋኑኤል ላይ የሚሰነዘረው ቅጣት የከፋ ይሆናል።

ሲያገባና ሲፈታ የኖረ ሰው ወደ ንስህ ሲመለስ ሊመነኩስ ይችላል። ምንኩስናውንም ቢፈልግ ሊጠብቀው፤ ቢፈልግም ሊጥለው ይችላል። ወደ ቅስና አገልግሎት ልምጣ ካላለ በቀር አይወቀስበትም አይከሰስበትም። ምንኩስናው የግሉ ነው። ቁምስና ደግሞ ከረዥም የአገልግሎት ዘመን በእርግናና በበኩርነት የሚከሰት ነው። በሽምግልና ዘመኑ ባካበተው ልምድና ጥበብ በገዳማትና በጽጽስና መካከል ለሚደረግ ተልእኮ የሚሰለፍ ነው። አሁን ባሉበት ሁኔታ ላይ በቅስና አገልግሎት ለሚቃወማቸው ህዝብ ቆሞስ አርጎ የቀድሞውን ቄስ ታደሰ ሲሳይን ወደ ህዝብ መላክ ምእመናን መበተንና ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን እንዳልነበረች የሚያደርግ ተግባር ነው። አባ ፋኑኤል ይህን በማድረጋቸው ከግለ ሰቡ ጋራ በተመሳሳይ ባህርይ ላይ መኖራቸውን በራሳቸው በማረጋገጣቸው ቅስናን አዋርደዋል። የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንንም ክብር ደፍረዋል።

በአባ ፋኑኤል ላይ ቤተ ክርስቲያናችን የምታዝዘውን ቅጣትና ተግሳጽ ለማሳለፍ ኃላፊነቱን የሚወስድ ከጠፋ፤ ከላይ የገለጽነውን ገጸ ንባብ መመሪያችን አድርገን፤ አባቶቻችን ሊቃውንት ያስተማሩንን በአባ ፋኑኤል ላይ ተግባራዊ አድርገን **በቤተ ክርስቲያችን ለተጠመቀ ሁሉ እናቀርባለን። የምናቀርበው ከመመሪያችን የራቀና ትክክል ሆኖ ካልተገኘ "ወእመ አኮሰ ለይሰየም ወእድዉኒ ወኢያቀመ ላዕሌሁ ዘዘከሮ ለእመ ኮነ ህዝባዌ ለይትገሰጽ በከመ ይደሉ፤ እመሂ ኮነ ካህን ለይሰደድ እምቤተ ክርስቲያን"( 99) በሚለው መመሪያችን መሰረት በአባ ፋኑኤል ላይ የምናቀርበው ክስ፤ ወቀሳ፤ ውግዘት በኛ ላይ ቢፈጸምብን በደስታ ለመቀበል ራሳችንን አዘጋጅተናል።**

ንብረት ለመዝረፍ የገበያን ግርግር እንደሚናፍቅ ሌባ፤ መከፋፈላችንን እንደ ትልቅ አጋጣሚ ተጠቅመው "ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል፤ መፋታትን እጠላለሁ ይላል እግዚአብሔር" (ሚል 2፡16) የሚለውን እንድናስተምርበት የተቀበልናትን ቅስና ሰጥተናችኋል በማለት አስርገው በማስገባት ላይ ያሉትን አዳዲስ ተከል የሆኑትን ጳጳሳት ለመቃወም: ለመገሰጽና: ለማውገዝም ቅስናችንን እንድንጠቀም ቀኖናችን ይፈቅድልናል።

የመጀመሪያ ሚስታቸውን የልጆቻቸውን እናት እያሰቃዩ የፈቱና ሌላዋን እያገቡ የወለዱ ሁሉ፤ ቆብ እየደፉ፤ በቅስና በምንኩስናና በቁምስና ስም ራሳቸውን ሸፍነው ያላንዳች ታዛቢ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሚፈጽሙትን ደባ ላለማየት ህዝበ ክርስቲያን ሲበተን እያየን አይመለከተንም ብለን ዝም ማለት፤ ግርግሩን ተጠቅመው ገንዘብ ለመሰብሰብ ሰርስረው ከገቡት ከነ እነ አባ ፋኑኤል የተሻልን አለመሆን ነው።

ይህን የመሰለውን ደባ እያየን አያገባንም ብለን ዝም ጭጭ ማለት፤ ለታላቋ ቤተ ክርስቲያናችን ግድ የሌለንና ማንም እንደፈለገው ቢፈነጭባት ምንም የማይሰማን ሆነን መገኘት፤ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት አበው ጉባዔ ተምረን ሳናልፍ ሰብረን የገባን ወራሪዎችና ምንደኞች ያደርገናል። አቡነ ማትያስና ሲኖዶስ ከፈቀዱለት እግዚአብሄር ይቅጣቸው እንጅ እኛ ምናገባን በማለት፤ ይህን ላለማየት የሸሻችሁ፤ በቤታችሁም ዘግታችሁ የተቀመጣችሁ፤ ህሊናችሁ ከሚጸየፋቸው ጋራም የተሰለፋችሁ፤ ከውሳኔ ላይ ለመድረስ ይረዳችሁ ዘንድ፤ በቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይ ላይ የተላለፈባቸውን የውግዘት ውሳኔ 5 ገጽ እና በተጨማሪ ስለ አባ ፋኑኤል ስህተት የተጻፈውን 10 ገጽ ተጨማሪ ሰነዶች ከዚህ መሸኛ ጋራ በማያያዝ በየአድራሻችሁ ልከናል።

በተረፈ፤ "ወአብዝሃ ለዛቲ ዓጸደ ወይን፡ እንተ ተከልካ በየማንከ ቅድስት" እያለን የምንማጸነው እግዚአብሔር የተናወጠውን የቤተ ክርስቲያናችንን አንድነት መልሶ ይገንባልን!

ሊቀ ማዕምራን ዶ/ር አማረ ካሳዬ

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

አባ ኃይለ ሚካኤል ወልደተክለሃይማኖት

ግልባጭ:-

- ለሲኖዶስ ጽ/ቤት
- ለልዩ ጽ/ቤት
- ለሊቃነ ጳጳሳት

  በየአህጉረ ስብከታቸው

- በሰሜን አሜሪካ ለሚገኙት አድባራት
- በካናዳ ለሚገኙት አድባራት
- በአውሮፓ ለሚገኙት አድባራት
- በአውስትራሊያ ለሚገኙት አድባራት
- በደቡብ አፍሪካ ለሚገኙት አድባራት

  በያላችሁበት ይድረሳችሁ

ለምንወደዎ ወንድማችን ታደሰ ሲሳይ፡-

Hamere Noah Kidane Meheret Ethiopian Orthodox Tewahido Church
75 South Bragg Street,
Alexandria, Virginia 22312.

March 10, 2014

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን።
ወንድማችን ሆይ፡-

የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም እንዳይለየዎ እንጸልያለን።

ከኛ የበለጠ የሚያውቁት ችግር በዚህች አባሪ በተ ላከለዎ ሰነድ ባጭሩ ተገልጿል። "ውሸትን አስወግዳችሁ እርስ በርሳችሁ ብልቶች ናችሁ። እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋራ እውነትን ተነጋገሩ ። ተቆጡ ኃጢአት አታድርጉ። በቁጣችሁ ፀሀይ አይግባ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት (ኤፌ 4፡25-27) ያለውን በመከተል ከርሰዎ ጋራ ከፉና ደግ ያሳለፉ ወገኖ ችዎ ምእመናን በሽምግልና እንዲያልቅ ደጋግመው ያቀረቡልዎትን ጥያቄ ባለመቀበልዎ እራሰዎ ለዲያብሎስ ትልቅ እድል በመከፈት ሁላችንንም አስጨናቂና ፈታኝ በሆነ ችግር ውስጥ እንድንገባ በማድረገዎ እጅግ አዝነናል።

ይሁን እንጅ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ያፍር ዘንድ ከእርሱ ጋራ አትተባበሩ። ነገር ግን እንደወድም ገስጹት እንጅ እንደጠላት አትቁጠሩት" (2ኛ ተሰ 3፡14) ብሎ የሰጠውን መመሪያ መሰረት በማድረግ፤ የምንቀድስበትን መጽሀፍ ያዘጋጀው ቅዱስ አትናቴወስ "ገስጽዎ ለኃጥእ ከመ እኍክሙ ዝልፍዎ በግህደት ለእመ ቦቱ አበሳ" ቁ 9 ብሎ በአጽንኦ ያስጠነቅቀንን ተግባራዊ ሳናደርግ ብንቀር የሚደርስብንን የህሊና ወቀሳ ልንቋቋመው አለመቻላችንን ሊረዱልን ይገባል።

እኒህንና የመሳሰሉትን መመሪያዎቻችንን በመከተል በርሰዎ ላይ በገሀድ ያሳለፍነውን ውሳኔ ስንጀምር ተጨንቀናል። ያማከርናቸው የቅርብ ጓደኞዎች ሁሉ ቅስናውን ክብር መንካት ነውና ተውት ከማለት በቀር፤ "ታደሰ ይህን የሚያደርግ አይደለም" የሚል አንድ ሰው አልገጠመንም። ተው ብለው የመከሩዎ እውነተኞች ወንድሞች የነበሩወት አይመስለንም። ካሉም ያመስግኗቸው እንጅ አይጥሏቸው። እኛም ይህን ውሳኔ ስንወስን ራሳችንን ከህሊና ወቀሳ ለማዳን፤ እርሰዎንም ወደ ንስሀ ለማምጣት ብቻ እንጅ ከርሰዎ ጋራ የግል ጥላቻ እንደ ሌለን ራሰዎ ያውቃሉና ሊጠሉን አይገባም።

በተጨማሪም የምንገልጽለዎ፤ በስመዎ ያስመዘገቡት ንብረት እና ከወታደር ዱላ ሸሽቶ ከኢትዮጵያ የመጣውን ህዝብ ለማበረር የታጠቀ ወታደር የሚቀጥሩበት ገንዘብ የተሰበሰበው ከዚሁ በወታደር ከሚያስፈራሩት ህዝብ ነው። ካገራችን ከኢትዮጵያ አንዲት ሳንቲም ይዘው እንዳልመጡ ያውቃሉ። ፈቃደዎ ቢሆን እስካሁን የሚያደርጉትን አቁመው፤ ላደረሱት በደል ይቅርታ ይጠይቁ። በስመዎ ያለውን ንብረት ለተቀዋሚዎቸዎ ክርስቲያኖች አስረክበው የሰነዘርንበወትን ውግዘት ሊፈታለዎ ወደ ሚችል ስልጣን አቅርበው ውሳኔውን አሽረው ቢመለሱ፤ የቤተ ክርስቲያናችን ህግ ነውና ምእመናኑ እጃቸውን ዘርግተው እንደሚቀበሉዎ አረጋግጠናል።

መቀደስ በሚያስችል ሁኔታ ችግሩ ባይፈታም እንኳ፤ ለሰሩት ስህተት ንስሀ ገብተው ቢመለሱ ክብረዎ ተጠብቆ ቤተ ክርስቲያንዎን በሌላ መስክ ማገልገል የሚችሉበት መንገድ እንደሚከፍትለዎ ቃል እንገባልወታለን።

በመከርነዎ መንገድ ችግሩን ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ እስካሁን በሄዱበት መንገድ ቢቀጥሉ ትግሉ ከተቃወመዎት ምእመናን ጋራ ብቻ ሳይሆን ከእምነቱ ከባህሉና ከኢትዮጵያዊነተዎ ጋር መሆኑን እንዲረዱና የተረፈችውን ፍቅርና ርህራሄ ከሁላችንም ህሊና ጨርሰው እንዳያጧት እንማጸነዎታለን። ያሳለፍነውን ውግዘት በቅዱሳት መጻህፍት መዝኖ ያነሳዋል ብለው ለሚያምኑት አካል ለማቅረብ የሚመኮሩ ከሆነና ከኛ እርዳታ ከፈለጉ፤ ልንረዳዎ ፈቃደኞች መሆናችንን ቃል በመግባት፤ ክርስቶስ በተወልን ሰላምና ይቅርታ በዚች መሸኛ ደብዳቤ ያሳለፍነውን 4 ገጾችን የያዘ የውግዘት ሰነድ ልከንልወታል።

በተረፈ "እመኒ ወደቁ ውስተ ጽልመት፤ እግዚአብሄር ያበርህ ሊተ" እያሉ ያለፉት ያባቶቻችን ቀሳውስት አምላክ ሁላችንንም በወደቅንበት ጨለማ ብርሃኑን ያብራልን !

ወንድሞችዎ 1ኛ ሊቀ ማእምራንን ዶክተር አማረ ካሳዬ
2ኛ ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ
3ኛ አባ ኃይለ ሚካኤል ተክለሃይማኖት

# በቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይ ላይ በምእመናን እና በሶስት ቀሳውስት የተላለፈ ቃለ ውግዘት

Comfort Inn
6254 Duke St, Alexandria, VA 22312
USA
March 10, 2014
(እሁድ የካቲት 30 ፳፻፮ ዓ.ም.)

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አህዱ አምላክ አሜን።

## ለመላው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን:

በቨርጅንያ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የነበሩት ቄስ ታደሰ ሲሳይ በተደጋጋሚ የፈጸሙትን ስህተት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ወንድምህ ቢበድልህ አንተና እሱ ሆናችሁ ውቀሰው ። ቢሰማህ ወንድምህን ጠቀምከው ። ባይሰማህ ግን በሁለት ወይም በሶስት ምስክር አፍ፤ ነገር እንዲጸና ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋራ ውሰድ። እነርሱንም ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት።” ባለው መሰረት መሸከም የከበዳቸው ምእመናን፤ ሀላፊነታቸውን ለመወጣት ለሚመለከተው አካል ሁሉ ድምጻቸውን አሰሙ።

ቄስ ታደሰ በክርስትና መመሪያችን መሰረት ለሰላምና ለይቅርታ ከመዘጋጀት ይልቅ፤ ለምን አጋለጣችሁኝ በሚል መንፈስ ተበቅለው፤ ምእመናንን ከፋፈሉ። ንብረቱን በስማቸው ስላስመዘገቡት ብቻ ከራሳቸው ከምእመናኑ በሰበሰቡት ገንዘብ ወታደር እየቀጠሩ የተቃወሟቸውን ምእመናን ከቤተ ክርስቲያን አንድ ባንድ ማባረር ጀመሩ። ያካባቢውን ተመልካች ኢትዮጵያዊነትን እንዲታዘብ ቢያደርግም፤ ምእመናኑ ምርጫ በማጣታቸው የጀመሩትን ተቃውሞ ሳይሰለቹ በየሳምንቱ ቀጠሉ።

ድምጻቸው በዋሽንግተን ዲሲ፤ በሜሪላንድና በቨርጅንያ ላለው ህብረተ ሰባችን አስተጋባ። ቄስ ታደሰ ሲሳይ ስህተታቸውን አርመው በሰላም አገልግሎታቸውን እንዲቀጥሉ በሽምግልና እንዲያልቅ ሽማግሌዎችን ልኮባቸው የነበረው ህዝብ፤ እንደገና ተሰብስቦ በኛ ታዛቢነት ከመካከላችን ይወገዱልን የሚል ውሳኔ አሳለፈ።

ይህን ህዝባዊ ድምጽ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን መጻህፍት ስንመዝነው፤ ቄስ ታደሰ ሲሳይ እጅግ ርቀው በመሄድ ተሳስተዋል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን አስነቅፈዋል። ኢትዮጵያዊውን ቅስናችንንም ከትችት ላይ እንዲወድቅ አድርገዋል። የቄስ ታደሰን ተደጋጋሚ ስህተትና ምእመናኑ የከፈሉትን መስዋዕትነት በሩቅ እንደሚመለከት ባእድ ታዛቢ መስሎ መመልከት ከእምነትና ከሞራል ውጭ መሆናችን ተሰማን። ምእመናኑ የደረሰባቸውን ውጣ ውረድ በትእግስት ችለው የወሰዱትን ርምጃ እያደነቅን፤ ቤተ ክርስቲያናችን በሰጠችን የቅስና ስልጣን በቄስ ታደሰ ሲሳይ ላይ “እንደ አረመኔ እንደ ቀራጭ ይሁንልህ (ማቴ 18፡ 15-18 )” ብሎ ክርስቶስ ያዘዘውን ተግባራዊ አድርገናል።

## ለካህናት የተሰጠ ኃላፊነት

በቅስና ተልእኮችን መጀመሪያ “ወእፎ እንከ ዘኢትሜህር ርእሰከ ዘለባእድ ትሜህር። ኢትስርቅ ትብል ወለሊከ ትሰርቅ፡ ኢተዘሙ ትብል ወለሊከ ትዜሙ፤ ወተሀውር ኅበ ብእሲተ ብእሲ” (ሮሜ፪ ፡፳ ፪) ይህም ማለት፡- “እራስህ እየሰረቅ እየዋሸህ እየዘሞትክ ሌላውን አትስረቅ ብለህ እንዴት ማስተማር ትችላለህ? ራስህን ሳታስተምር እንዴት ሌላውን ላስተምር ትላለህ?” የሚለው ሐዋርያዊ ቃለ-ተግሳጽ ራሳችንን እንድንፈትሽ ተምረናል።

ቅዱስ አትናቴዎስም፤ ይህን ሀዋርያዊ ግዴታ መሰረት አድርጎ "ኦ ካህናት አንትሙ ውእቱ አዕይንተ እግዚአብሔር ብሩሀት ተናጸሩ በበይናቲከሙ አሀዱ ምስለ ካልዑ። ሕቱ እምውስተ ሕዝብከሙ በአበይኖ። ኢይቁም ወኢይህበር ምስሌከሙ በጸልዮ ኢዘማዊ ወኢቀታሊ ኢሰራቂ ወኢሀሳዊ"። ይህም ማለት "እናንት ቀሳውስት (ካህናት) እግዚአብሄር የሚወደውን ለመከተል የሚጠላውን ለመሸሽ እንድታስተውሉ የእግዚአብሔር አይኖች ናችሁ። በመጀመሪያ እርስ በርሳችሁ ተራረሙ። በመካከላችሁ የሚሰርቅ የሚዘሙት የሚዋሽ የሚገድል ከናንተ ጋራ እንዲጸልይ አትፍቀዱ። ከዚያም በኋላ በህዝቡ መካከል የተከሰተውን ስህተት እግዚአብሄር በሚፈቅደው መንገድ አርሙ" ብሎ ለቀሳውስት የሰጠውን መመሪያ ተምረናል። በዚህ መርሆ የዚህች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን በገጠር በከተማ የነበሩ አባቶቻችን ቀሳውስት እርስ በርሳቸው እየተራረሙና በህዝባቸው መካከል የሚከሰተውን ከህዝባቸው ጋራ እየተናጋገሩ የሚወገዘውን እያወገዙ የሚፈታውን እየፈቱ ኢትዮጵያን የሞራልና የስነምግባር ምንጭ አድረገዋት መኖራቸውን ታሪካችን ያረጋግጣል።

ህዝባዊ የሆነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የቅስና አገልግሎት በሐዋርያት ስራ ምእራፍ 20 ከ ቁጥር 17 እስከ 35፤ በተለይም ከቁጥር 15 እስከ 19 ላይ ተመዝግቦ እንደምናነበው ቅዱስ ጳውሎስ የመጨረሻውን አደራ የሰጣቸው በነዚህ ቦታዎች ይኖሩ ለነበሩት ቀሳውስት ነው።

ይህን ሐዋርያዊ ትውፊት የተረከቡት ከተቀደሰው ጋብቻ ውጭ የነበሩ ቆሞሳትና መነኮሳት አልነበሩም። በቁጥር 28 ላይ ጳጳስ የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን ዛሬ ከተበላሸው በፊታችን ቆመው በምናያቸው አንዳንድ መነኮሳት ራስ ላይ ያለ ቢመስልም፤ ምንኩስና በትዳር ተወስኖ የሚሰጠው አገልግሎት ያላረካቸው ሰዎች የሚገቡበት ግላዊ ምርጫ ነው። ምንኩስና በመጀመሪያ ከዚህ ዓለም ምኞት ሥጋዊ ፍላጎት ሸሽቶ ራስን ለማዳን ከዓለም ራስን ቆርጦ ለመጣል የሚየደረግ ውሳኔ ነው። ምንኩስና የግል መሳሪያነቱ ከግለ ሰቡ ጋራ ተስማምቶ በምንኩስና ዘመኑ የሰበሰበው ትሩፋቱ ለህዝብ መጥቀም መቻሉ ሲረጋገጥ ብቻ እንጅ፤ የህዝብ መገልገያ ህዝባዊ ንብረት ሆኖ የተሰጠው ቅስና ነው።

በሞቱና በትንሳኤው ከጌታችን ጋራ ወደ ክርስቶስ የሚመጡትን አንድ ለማድረግ ቀሳውስት ያጠምቃሉ። ሙታንን ይፈታሉ። <u>"ከመ ንፍታህ ዘኢይትፈታህ"</u> እያሉ የሚጸልዩትን ኪዳን በተግባር ይተረጉማሉ። "ከኃጢአት ከመርገምም ከበደልም ከክህደት ከመገዘት በሐሰት ከመማል አድነን" ብለው በሚያቀርቡት ተግሳጽ አዘል ጸሎት የህሊናቸውን ዳኝነት ይጠብቃሉ።

እንድናከናውንበት የተሰጠን የቅስና ክህነት በአንዲት ጥምቀት በአንዲት ሃይማኖት ላይ የተመሰረተ ነው። ክህነት አንዲት ናት። የምንገለገልባቸው መጻሕፍት አንድ ናቸው። ስርዓት አልባ (anarchy) ተፈጥሮ ምእመናን እንዳይበታተኑ ቀሳውስት ክህነት እንዳይሰጡ ብቻ ይታገዳሉ። የቀረውን ሲፈቱና ሲያስሩ የኖሩት ቀሳውስት ናቸው። በዚህ ሀላፊነታችን በቨርጅንያ ሀመረ ሆህ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን በተፈጠረው አሳሪና ፈች ችግር፤ የሚታሰረውን አስረን የሚፈታውን ለመፍታት ዛሬ በዚህ ቦታ ተገኝተናል።

## <u>የውግዘት ምንጭና መነሻ የተወጋገዡ ግለሰብ ባህርይ ነው።</u>

ውግዘት ከየትም የሚመጣ አይደለም። የውግዘት ምንጭና መነሻ የተወጋገዡ ግለሰብ ባህርይ ነው። አውጋዥ የተበከለችው እውነት እና በግለ ሰቡ ስህተት የተጎዳው ህዝብ ነው። የቅስና ተልእኮ ቢቻል ማስታረቅ ካልተቻለ የውግዘቱ መሰረት የሆነውን ግለሰብ ለይቶ የቀረበበትን ስህተት በቅዱሳት መጻህፍትና በባህላችን መዝኖ መወሰን ነው። በዚህ መሰረት የቀድሞው ቄስ ታደሰ ከዚህ በታች የፈጸሚቸውን ስህተቶች ለማረምና ለማስተካከል በተደጋጋሚ የቀረበላቸውን ጥያቄ ባለመቀበላቸው ይህ ውግዘት ከራሳቸው እምቢተኝነት የመነጨ ነው።

### <u>የውግዘቱ ምክንያት</u>

1ኛ:- አሁን ከደረሱበት ውድቀት ላይ በጣላቸው አስከፊ ባህርያቸው የልጆቻቸውን እናት በመፍታታቸው ቤተ ክርስቲያንን አስነቅፈዋል።

2ኛ:-ከሌሎች ሴቶች ጋራ በተደጋጋሚ በሚፈጽሙት ከቄስ የማይጠበቅ ዝንባሌና ስሜት በማሳየት በተደጋጋሚ በህበረተ ሰቡ ሲወቀሱ ይሰማል።

3ኛ:- በቤተ ክርስቲያናችን ህግ አንድ ቄስ ህጉ በህይወት እያለች ፈቶ ወይም ትዳሩን አፍርሶ መመንኮስ ክልክል ነው። ቄስ ታደሰ ህጋቸውን ካፈረሱ በኋላ ቢመነኩሱም ህይወታቸውን በንስሀ ሆነው በሌላ ተልእኮ ካልሆነ በቀር

ቀድሰው ማቁረብ አይችሉም።

4ኛ ከአቶ ቴወድሮስ አደፍርስ ባለቤት ጋራ በፈጸሙት አስነዋሪ ባህርይ ራሳቸው አቶ ቴወድሮስ ለቄስ ታደሰና ለሴትይዋ መሳሳታቸውን እንዲያቆሙ ነግረዋቸዋል። የከፍሉ ጳጳስ ነኝ ለሚሉት ለአባ ፋኑኤልም ነግረው "ካቅሜ በላይ ስለሆነ ወደ ህግ አቅርበው በማለት ሸኘተዋቸዋል። አቶ ቴወድሮስም ለመላው ህብረተ ሰብ በህዝብ መገናኛ ለጠቅላላው ህዝብ ብሶታቸውን ገልጸዋል። ቄስ ታደሰ የሚፈጽሙት ስህተት ባለማቆማቸው ወደ ልጆች እንዳይደርሱ በአሜሪካ ፍርድ ቤት ታግደዋል። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በልጆቻቸው ፊት የሚያደርጉትን አስነዋሪ ግንኙነታቸውን አላቆሙም። አቶ ቴወድሮስም ይህ አስነዋሪ ተግባር የልጆቻቸውን መንፈስ ስለጎደው፤ ልጆቻቸው ከተወለዱበት አገራቸው ካሜሪካ እርዳታና የህሊና መረጋጋት ለማግኘት ወደ አፍሪካ ይዘው እንዲሄዱ ተገደዋል።

5ኛ፡-በቅዱሳት መጻሕፍትና በባህላችን እንኳን ቄስ ነኝ የሚል ሰው፤ ለዚህ አገልግሎት ለምሳሌነት የማይጠቀስ ምእመን እንኳ፤ ሁለት ሶሶስት ሰዎች ስህተት አየንበህ አቁም ካሉት፤ ራሱን ገለል አድርጎ በስህተት መበደሉን ለሚመለከተው ማቅረብ ባህላችን ነው። እሳቸው ግን በወታደር ያባረሯቸውን ምእመናን የሚሊዮን ብር ካሳ ይከፈለኝ ብለው ወደ አደባባይ ገሰገሱ። ይህም የሚያሳየን ቅስናውን ለገንዘብ እንደሚጠቀሙበትና ለገንዘብ ፍቅር ያበዱ መሆኑናቸውን የሚያሳይ የበለጠ ካገልግሎት እንዲገለሉ የሚያደርጋቸው የከፋ ስህተት ነው። በነዚህና በመሳሰሉ ስህተቶቻቸው ከዛሬ ጀምሮ በቅስናቸው እንዳይጠቀሙ የህዝቡን ውሳኔ "ይቀበለው እግዚአብሔር" ብለን በማጽደቅ በቅስናቸው የሚሰጡትን አገልግሎት አግደናል።

## ለምእመናን ማሰሰቢያ

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "በከመ ተጋብአት ዛቲ ህብስት እንዘ ዝሩት ይእቲ ማእከለ አድባር ወአውግር ወውስተ ገዳም ወቆላት ወተጋቢአ ኮነት አሐተ ጽርስፎራ ፍጽምተ ወከማሁ ኪያነሂ አስተጋብአነ በመለኮትከ እምኵሉ ሕሊና እኩይ ዘኃጢአት ውስተ ሃይማኖትከ ፍጽምት " (ገጽ ፻፺፩፡ ፺፩) እንዳለው ማለትም፡- "በቆላ በደጋ በሸለቆ በተራራ የተዘራችው የስንዴ ቅንጣት ተሰብስባ አንድ ህብስት እንደምትሆን፤ እኛንም ከተለያዩ ቦታዎች ቋንቋዎች ባህሎች በመለኮትህ ሰብስበን፤ ከክፉ ማሰብና ስራ ለይተህ አንድ አድርገን።" ብለን እንጸልያለን።

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምስጢረ ቁርባን የምንማረውና የምናስተምረው፤ ለቁርባን የምንሰይማት አንዲት ህብስት የተሰራችባቸው የሰንዴ ዛላዎች፤ ቅንጣቶች፤ ፍሬዎችና የዱቄትነታቸው መበታተን በውህ ተዋህዳ አንዲት ህብስት ትሆናለች። ይህች አንዲት ህብስት በተዋህዶ ክርስትና እምነት የተጠመቅነውን የኢትዮጵያውያንን አንድነት ትወክላለች። እኛን ኢትዮጵያውያንን ብቻም አይደለም፤ በዜግነት በቋንቋና በባህል ከማንገናኛቸው በተዋህዶ እምነት ከሚተባበሩንና ከሚመስሉን: ከግብጾች ከህንዶች አርመኖችና ከሶርያዎች ጋራም ያለንን አንድነት ትወክላለች።

## <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የቤተ ክርስቲያናችን አካላት የሆናችሁ ሁሉ</u> !

ከላይ በምሥጢረ ቁርባን እምነታችን የተገለጸውን ቀጥታ ከመጽሐፉ ባትጠቅሱትም ከቆራቢዎች እናት አባቶቻችሁ ስትሰሙት በመኖራችሁ ባህል ሆኖ በደማችሁ ገብቷል። በዚህ ባህል በየደረሳችሁበት ማንነታችሁን ገልጻችሁ ባትመዘገቡም፤ ባካባቢ ያለውን ህዝብ የራሳችሁ አካል፤ የተሰሩትን ህንጻወች፤ በስለት የተሰበሰቡትን ነዋየ ቅድሳት ሁሉ የኔ ናቸው ብላችሁ በማሰባችሁ የተጠየቃችሁትን ሁሉ ገንዘብ በደስታ ትሰጣላችሁ።

በምሥጢረ ቁርባናችን ያለውን ይህን የተቀደሰ ልማድ ብንወደና ብናከብረውም፤ አገር ለቀን ስንሄድ አንዳንድ መስለው የገቡ ሰዎች ሳትጠራጠሩ የሰጣችሁትን ገንዘብ ለግላቸው መብለጸጊያ እያደረጉት ነው። ባህላችሁን በመከተል ገንዘባችሁን ስትሰጡ እነዚህ ሰብሮ ገብ አስመሳዮች ቀሳውስት ስቀው ይቀበላሉ። ገንዘቡ እንደባከነ ተጠራጥራችሁ ጥያቄ ስታነሱ የሰጣችኋቸውን የተቀበሉ እነዚሁ አስመሳዮች አልተመዘገባችሁም ብለው በፖሊስ ያባርሯችኋል። ይህ ነገር አስመስለው ለገቡ አመቺ፤ ለመንግስት ውሳኔ አስቸጋሪ ስለሆነ ሁላችንም ልናስብበት ይገባል።

የሁለቱን ሲኖዶሶች መለያየት እንደ ገብያ ግርግር ለዘረፋችሁ የሚበጃችሁ አርጋችሁ የምትቆጥሩ አስመሳይ

ቀሳውስትም "የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ ? (ማቴ. 22፡12)" ብሎ ክርስቶስ መስለው ለሚገቡት አስመሳይ የተናገረውን ቃል እያስገነዘብን፤ በውግዘት "እጅ እግሩን አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት" ብሎ ክርስቶስ የተናገረው ወደ እናንተ እየገሰገሰ መሆኑን ልናሳስባችሁ እንወዳለን።

በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን በቀድሞው ቄስ ታደሰ የተከሰተው ችግር ባለንበት ዘመን በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ተንሰራፍቶ እየታየና ህዝባችንን እየበጠበጠ ነው። በአገራችን በኢትዮጵያ የሚታየው የመንግስት እጅ ስላለበት ከቁጥጥራችን የራቀ ቢሆንም፤ በውጭ አገር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚካሄደውን ብዝበዛ ለመቆጣጠር የሁላችንም ኃላፊነት ነው። በልማድ የምንከተለው ምስጢረ ቁርባኑ የሚገልጸውን ህብረታችንን ወደ ተግባር ለውጠን የኃጢአት ስር በተባለው ፍቅረ ነዋይ የሰከሩትን አስመሳዮች፤ ክርስቶ በቤተ ምኩራብ ያሳየውን ምሳሌ በመጠቀም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ለማጽዳት እግዚአብሄር ጥበቡንና ኃይሉን ይስጠን።

የችግሩን መነሻ ዝርዝር ከዚህ በመቀጠል በድረ ገጾች አማካይነት እናቀርባለን።


1. ሊቀ ማ ዕምራን ደ/ር አማረ ካሳዬ
   (ዋና አስተዳዳሪ)
   የርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም
   የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
   1350 Buchanan St NW, Washington, DC 20011

2. ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ
   (ዋና አስተዳዳሪ)
   ደብረ ሣህል መድኃኔ ዓለም
   የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
   1119 Lowell Avenue, Kansas City, KS 66102

3. አባ ኃይለ ሚካዔል ተክለሃይማኖት
   (ዋና አስተዳዳሪ)
   ደብረ ቅዱሳን አቡነ አረጋዊና ተክለሃይማኖት
   የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
   Arlington, VA

ኅዳር ፲፫ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም.

November 22, 2014

*<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ያለ አንዳች አድለዎ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማገልገል የተሰለፋችሁ የመገናኛ አውታሮች፤ ድረ ገጾች፤ የማህበርም ሆነ የግል ድርጅቶች የሆናችሁ ይህች መግለጫ ለእምነቱ ተከታይ ሁሉ ትደርስ ዘንድ በድምጻችሁ ሳይቀር እንዳታስተጋቡልን በትህትና እንጠይቃለን። እግዚአብሔር እነዚህን ከመሳሰሉት ውድቀቶች ሁላችንንም ይጠብቀን!*

# አባ ፋኑኤል ራሳቸውን ወጉ



*አባ ፋኑኤል በራሳቸው ላይ ደፊተውት በዚህ ፎቶ ግራፍ የሚታየው ፓትርያርካዊ አክሊል ፤ ወደፊ ት ፓትሪያርክ ለመሆን ባላቸው ምኞት ሲለማመዱበትና በየዓውደ ምሕረቱ ሲታዩበት ቆይተው ለአቡነ ማትያስ በስጦታ ያበረከቱት ፓትርያርካዊ ክሊል ነው።*

*(ዋሸንግተን ዲሲ 2006 ዓ.ም. )*

## መግቢያ

አቡነ ፋኑኤል በዜና ቤተ ክርስቲያን ላይ እንዲሰፍር ያደረጉት ሽፍጥ፤ ቢጤያቸውን ለመጋረድና የዘረጉትን የጥፋት መረብ ለማዳን ያደረጉት ሙከራ እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ነው። በዚህ ሽፍጥ ቢጤያቸውን ጋርደው ማዳን ይቅርና፤ ራሳቸውን ከቤተ ክርስቲያናችን አውጥተው መጣላቸውን ለማሳየት የምእመናኑን ውግዘት በቅዱሳት መጻህፍት መዝነው ካወጁት ቀሳውስት፡-

1. ሊቀ ማዕምራን ዶ/ር አማረ ካሳዬ
   የርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም
   የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ
   1350 Buchanan St NW, Washington, DC 20011

2. ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ
   የደብረ ሣህል መድኃኔ ዓለም
   የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ
   1119 Lowell Avenue, Kansas City, KS 66102

3. የደብረ ቅዱሳን አቡነ አረጋዊና ተክለሃይማኖት
   የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ
   701 South Highland Street, Arlington VA 22204

## የተሰጠ መግለጫ

የቨርጅንያ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምህረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የነበሩት የቀድሞው ቄስ መልአከ ኪዳን ታደሰ ሲሳይ የፈጠሩት ችግር በሰላምና በእርቅ እንዲያልቅ ብዙ ጥረት ቢደረግም፤ ራሳቸው አሻፈረኝ በማለታቸው "ወንድምህ ቢበድልህ በግሉ ምከረው ከሰማህ መልካም። ካልሰማህ ሁለት ሦስት ሰው ይዘህ ምከረው። ካልሰማህ ለቤተ ክርስቲያን ንገር። ቤተ ክርስቲያንን ካልሰማ እንደ አረመኔና ቀራጭ ይሁን" (ማቴ ፲፰፥፲፯ ) ብሎ ጌታችን በሰጠው መለኮታዊ ትእዛዝ ላይ የተመሠረተውን መመሪያ በመከተል መወገዛቸው ይታወሳል። [*ሙሉ ሀሳቡን ለማግኘት ይህን ሰንሰለት ይጫኑ፦ "በቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይ ላይ በምእመናን እና በሦስት ቀሳውስት የተላለፈ ቃለ ውግዘት"* ወይም ***ከዚህች መግለጫ መጨረሻው ገጽ ላይ ይመልከቱ***]።

አባ ፋኑኤል በአዲስ ተክልነት ባዶነታቸው ተገፍተው፤ በቀኖና ቤተ ክርስቲያናችን መሠረት ውግዘቱን የፈጸሙትን ምእመናንና እኛን ቀሳውስቱን በማይመለከታቸው ገቡ እያሉ በበራሪ ቀላጤ ወቅሰዋል። [*ሙሉ ሀሳቡን ለማግኘት ይህን ሰንሰለት ይጫኑ፦ "አባ ፋኑኤል ውግዘት ስለማንሳት የጻፉት"* ወይም ***ከዚህች መግለጫ መጨረሻው ገጽ ላይ ይመልከቱ።***]። በዚሁ በራሪ ወረቀት ውግዘቱን ደምስሰው ግለ ሰቡን ነጻ በማድረግ ወደ ቀደመ ክብራቸው ተመልሰዋል፤ እያሉ ራሳቸው ስተው ሕዝብን ለማሳት አዲስ አበባ በሚገኘው *ዜና ቤተ ክርስቲያናችን* ላይ ከግለ ሰቡ ፎቶ ግራፍ ጋራ አሳትመው በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን አጥር ላይ እንዲለጠፍ አድርገዋል። በዜና ቤተ ክርስቲያናችን ላይ አሳትመው የለጠፉት፦

፩ኛ፦ ጽሑፉ የውግዘቱን መነሻና መድረሻ ሳይገልጽ የተቆራረጠ ሽፍጥ ያዘለ ወሬ በመሆኑ ከሥር ላልተከታተለው ለኢትዮጵያ ሕዝብ መነጋገሪያ እንደሆነ ሰምተናል።

፪ኛ፦ ጉዳዩን ከሥር ጀምሮ በቅርብ በመከታተል ላይ ያለው በአሜሪካ የሚኖረው ሕዝበ ክርስቲያን ደግሞ በጋዜጣው ላይ የሰፈረው ነገር ከመሠረቱ ተቆርጦ የቀረበ አምታችና አወናባጅ በመሆኑ፤ ግማሹ ሕዝብ ጽጽስና በአቡነ ፋኑኤል ሞቶ ተቀበረ ባማለት፤ ግማሹ ጳጳስ ለእውነት ይቆማል ብለን እናምን ነበር፤ ለካስ ጳጳስ አይታመንም በማለት በምሬትና ተስፋ በማስቀረጥ እያበሳጨ እንዲነጋገርበት አድርጓል።

፫ኛ፦በኢትዮጵያና በአሜሪካ ያለውን ሕዝብ በውዥንብር ውስጥ የከተተና ቤተ ክህነቱንም ለግምት የዳረገ ይህ ሽፍጠኛ ጽሑፍ የዜና ቤተ ክርስቲያናችንን ክብርና ታማኝነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተንኮታኩቶ እንዲወድቅ አድርጎታል።

"ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው። አንዳንዶች ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ!" (፩ኛ ጢሞ ፮፥፲) እያለ ቅዱስ ጳውሎስ በተናገረው ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀው የቀኖናችን መጽሐፍ በግንባር ቀደምትነት ለሚያገለግሉት መንፈሳውያን ሰዎች የተዘረጋውን መመሪያ እየተነተነ መጥቶ፤ "እለሰ ያፈቅሩ ንዋየ ወይፈቅዱ ከመ ይብእሉ ይወድቁ ውስተ መንሱት ወመሥገርት ወፍትወት ብዝኀት፤ ዘታስህት ወታሰትም ሰብአ ውስተ ሐጉል ወሙስና። እስመ ሥርዉ ለኩሉ እከይ አፍቅሮ ንዋይ ( ፍ አ ፭፥፻፲፭) " በሚለው ሐዋርያዊ የማስጠንቀቂያ ትውፊት መርሆውን ደመደመ። ይህም ማለት "የክፋትና የጥፋት ሁሉ ሥርና ምንጭ ገንዘብ መውደድ ነውና፤ እጅግ መበልጸግ የሚናፍቁ በብዙ ዓይነት ውርደት ላይ ይወድቃሉ" ብሎ አምርሮና አጠንክሮ የተናገረው በአባ ፋኑኤል ተሽፈነ። ተደመሰሰ።

ቀኖና ቤተ ክርስቲያናችን በሚያዝዘው መሠረት በምእመናን ኅብረት የተወሰደውን ርምጃ፤ አባ ፋኑኤል አስተባብለውና ሸፋፍነው፤ ግለሰቡን ወደ ቀደመ ቦታቸውና ክብራቸው እንዲመለሱ ባደረጉት ሙከራ የፈጠሩት ችግር፤ አባ ፋኑኤል ውስጣቸው ሳይጸጽስ የጽጽስናውን ውጫዊ ሁለንተና ተላብሰው፤ ካልጸጸሰው ውስጣቸው የሚፈልቀው ሰይጣናዊ መንፈስ ፈንድቶ እንዲወጣ አደረገው። ካልጸጸሰው ውስጣቸው የፈለቀው ሸፍጥ የሰበረውን የምእመናን መንፈስ ለመጠገን፤ ዜና ቤተ ክርስቲያናችንንም ከወደቀበት ለማንሳት፤ ቤተ ክርስቲያናችንንም ወደ በለጠ ጉዳት ስለያሚያደርሳት አባ ፋኑኤል የፈጸሙት ስህተት የቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ ፈጽሞ የማይቀበለው መሆኑን ለመግለጽ ይህ መግለጫ አስፈለገ። ዝርዝር ሀተታውን ከዚህ በታች በገለጽናቸው ርእሶች አቅርበናል።

፩ኛ፡- አባ ፋኑኤል ራሳቸውን ወጉ
፪ኛ፡- በሕገ ወጥ አመራር ሕገ ቤተ ክርስቲያንን የሚቃረን ሥራ አልሠራንም
፫ኛ፡- የቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይን እንድናወግዛቸው የመራን የራሳቸው እኩይ ተግባር።
፬ኛ፡- ለወሰድነው እርምጃ መሠረታዊ መንደርደሪያ፤

## ፩ኛ፡-አባ ፋኑኤል ራሳቸውን ወጉ

የተቀደሰውን ትዳር በማፍረስ ያረከሱትን፤ በዝሙትና በተለያዩ ባህርያት በቤተ ክርስቲያን (ምእመናን) ተወግዘው የተባረሩትን ግለሰብ፤ አባ ፋኑኤል በመደገፍ የሠሩት ደባ የምመናን ልብ ሰብረዋል። የቤተ ክርስቲያናችን ክብር ከመሬት ጥለዋል። የተወገዘበትን ስህተት በተማርነው ነገረ መለኮትና ቀኖና መዝነን ያወገዝን እኛ የቤተ ክርስቲያኒቱ ቀሳውስት ቀርቶ፤ የውጭ ሰው እንኳ ስህተቱን በማረጋገጫ አስደግፎ ባላመንክበት በመሰለፍህ ከመመሪያህ ጋራ ተጋጭተሃልና ወድቀሃል ማለት ይችላል። አባ ፋኑኤል የተወሰደውን ርምጃ እየነቀፉ፤ የተወገዘውን እየደገፉ የጻፉትን ከግለ ሰቡ ፎቶ ግራፍ ጋራ *በዜና ቤተ ክርስቲያን (ቤተ ክህነቱ ጋዜጣ)* ላይ አሳትመው፤ በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት ቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ላይ መለጠፋቸው በደለኛውን ግለሰብ ሊያድኑ ሲሞክሩ ከጥንታዊት፤ ከሐዋርያዊትና ከታሪካዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጋራ በመጋጨት ራሳቸውን ወጉ።

ከግለ ሰቡ በፈለቀው ስህተት ምክንያት ማህበረ ምእመናን ተሰባስበው መክረውና አስመክረው የማይመለስ ሲሆን ቤተ ክርስቲያናችን ጽፋ በያዘችው ቀኖና ተለክቶና ተመዝኖ የተፈጸመውን ይህን የመሰለውን ውግዘት ይቅርና፤ የተሳሳተ ሰው በህዝባችን መካከል ሲከሰት፤ ማነኛውም የህብረተ ሰብ አካል ፤ "በሥላሴ በእግዚአብሔር ስም የምታደርገውን አቁም" ብሎ ማገድ የሚችል መሆኑ በባህላችን የተፈቀደ ነው። እነ አባ ፋኑኤል እንደሚያደርጉት በሀሰት ከሆነ ማቆም ይቅርና ያስቀጣል። ቤተ ክርስቲያናችን ያስተማረችን ይህንን ነው። ሥርዓታችንን ባህላችንን ጠልቀው ባለመረዳታቸው ሌሎች ዝም ቢሉም፤ ከሊቃውንት አባቶቻችን የተማርነው ከባህላችን የተረከብነው አደራ አባ ፋኑኤልና ያቆመሱት ግለ ሰብ የፈጸመውን ስህተት ታዝበን ለማለፍ አልፈቀደልንም።

ጥንታዊት፤ ሐዋርያዊትና ታሪካዊት እያልን የምንናገርላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ክህነት፤ በብዙ መንገድ የሚያስፈትን መስክ ነው።ከጥንታዊነቷ፤ ከሐዋርያዊትነቷ፤ ከመንፈሳዊነቷ ጋራ ከተዳመረው ሕዝቧ የሚፈሰው ክብርና ገንዘብ ለመሪዎቿ እጅግ ፈታኝ መስክ ነው። ይህም በመሆኑ በሲኦል ደጆች ሊታጠፍና ሊዘረጋ በማይችል ክርስቶስ በመሰረተላት ትጥቅ ሊቃውንቱን አዘጋጀች።ከዓለምና ፍላጎቷ ጋራ በዚህ መንፈሳዊ ትጥቅ ተዋግተው ፍላጎታቸውንና ዓለምን ድል የነሱ መንፈሳውያን ቀሳውስት ነበሩ። አሁንም በገጠር በከተማ ከህዝባቸው ጋራ መከራውን በመቀበል ታፍነው በመሰቃየት ይኖራሉ። በተቃራኒው፤ ፈተናውን ለመዋጋት የሚያስችሉትን ጥንታዊውን፤ ሐዋርያዊውንና ታሪካዊውን የመንፈስ ትጥቅ ሳይታጠቁ፤ የጽድቅ ቀጸላ ሳይቀዳጁ፤ የመዋጊያ ስልቱን ሳይረዱ፤ ከተከታዮቿ የሚጎርፈውን ክብርና የሚፈሰውን የገንዘብ ማዕበል አይተው በመጎምጀት ብቻ ዘለው የገቡ ብዙዎች ከዚህ በፊት እንደወደቁ፤ አሁንም እየወደቁ ናቸው። ሥጋዊ ፍላጎታቸውን ተዋግተው ከማሸነፍ ይልቅ፤ መስለው ገብተው በእጃቸው የያዙትን መስቀል ከመባረኪያነት ወደ መጥለፊያ ወጥመድነት፤ የደፉትን ቆብ ወደ ገንዘብ መሰብሰቢያ ዕንቅብነት ሲለውጡ የተሸከሙት መንፈሳዊ ሥልጣን ባርቆ ራሳቸውን ወግቶ ገደላቸው። ኃላፊነቱ ከችሎታቸው ከእውቀታቸው ከልምዳቸውና ከዕድሜያቸው በላይ ሆኖ እጅግ ስለ ከበዳቸውም መሸከም አቅቷቸው ወደቁ !

ቤተ ክርስቲያናችንን ጥንታዊት፤ ሐዋርያዊትና ታሪካዊት የሚያደርጋት ሐዋርያዊው ቅዱስ ጳውሎስ (1 ጢሞ 3፡6) ላይ የተናገረውን ሐዋርያዊ መርሆ ተከትላ፤ "ኢይኩን ተክለ ሐዲስ ከመ ኢይትዐበይ ወኢይደቅ ውስተ ፍትሐ ዲያብሎስ" ፱፡፪፻፹፫ ወኢውስተ አህባለ ሰይጣን" (አንቀጽ ፩፡፫፻፴) ማለትም፡- "በዲያብሎስ ወናፍ (ትእቢት) በመነፋት በፍርድ አደባባይ ቤተ ክርስቲያናችንን ይዞ እንዳይወድቅ አዲስ ሰው በአመራር ላይ አይሰለፍ"። እያለች የሰጠችው ማስጠንቀቂያ፤ የአባ ፋኑኤል አወዳደቅ ዓይነት እንዳይከሰት በየዘመኑ የሚነሳው ትውልድ ጥንቃቄና ጥረት እንዲያደርግ ነበር።

በሊቃውንቱ ሳይገራ፤ በመንፈሳውያን ሰዎች ሳይሞረድ በጥንታዊት፤ ሐዋርያዊትና ታሪካዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ለአገልግሎት በግንባር ቀዳሚነት መሰለፍ፤ የሚያስከትለውን አደጋ ሳይረዳ የተሰለፈ ሁሉ፤ ጥይት በጎረሰ ጠበንጃ ሲጫወት ባርቆ እንደተገደለ ሰው መሆን ነው። በነ አባ ፋኑኤል ላይ የተከሰተው ይህ ነው። አባ ፋኑኤል አሁን ካሉቡት ደረጃ ለመድረስ የሚያበቃቸውን የእውቀት ደረጃዎች ባለማለፋቸው የተሸከሙት ሥልጣን ባርቆ ራሳቸውን ገደላቸው። <u>ይህም ማለት ከነበሩበት ማዕርግ ራሳቸውን በራሳቸው ገፍትረው በመጣል፤ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን አገለሉ።</u>

በቨርጅንያ ኪዳነ ምሕረት ተጀምሮ እስከ ደረሰበት ያለውን የተደራረበ ስህተትና የተካሄደውን ሁሉ ደባ አባ ፋኑኤል ደብቀው፤ የራሳቸውን ስሜት ብቻ ለ*ዜና ቤተ ክርስቲያን* ጋዜጣ በማቅረባቸው፤ ራሳቸውን ብቻ ገፍትረው አልጣሉም። ጉዳዩን በቅርብ ሲከታተል የነበረ ሁሉ፤ ያሰራጩት የሐሰት ጽሑፍ ከተወገዘው ግለ ሰብ ፎቶ ግራፍ *በዜና ቤተ ክርስቲያን* ላይ ታትሞ መቅረቡን ሲያይ፤ በጥንታዊት ሐዋርያዊትና ታሪካዊት በምንላት ቤተ ክርስቲያናችን ላይ የነበረውን ክብር ከጥያቄ ላይ እንዲጥለው አድርገዋል። ይህም ስንት ሊቃውንት ላፈሩችው ቤተ ክህነታችንም ውድቀት በመሆኑ፤ አባ ፋኑኤል ይቅርታ የሌለው እጽፍ ድርብ ደባ።

፩ኛ፡- "መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው" በሚለው ላይ ተመስርቶ እውነት ማንጸባረቅ ያለበትን *ዜና ቤተ ክርስቲያን* ለራሳቸው ስሜት ማንጸባረቂያ በማድረጋቸው ክብሩን አዋርደዋል።

፪ኛ፡- የአባ ፋኑኤል ቢጤ የሆኑት ግለ ሰብ፤ በቨርጅንያ ኪደነ ምህረት ሕዝበ ክርስቲያን እንዴት እንደታገዱና በመጨረሻም ከክብራቸው እንዴት እንደተባረሩ ለማያውቀው በሩቅ ላለው ለኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ደረጃ በደረጃ የተፈጸመውን ውግዘት ሳይገልጹ በደፈናው "ወደ ቀደመ ክብራቸው ተመልሰዋል" የሚል ሽረኛ ጽሁፋቸውን፤ በ*ዜና ቤተ ክርስቲያን* ታትሞ እንዲቀርብ ማድረጋቸው፤ ሕዝበ ክርስቲያኑን ግራ ከማጋባት አልፎ፤ የተከበረውን ዜና ቤተ ክርስቲያን ለግለ ሰቡ ገበና መሸፈኛ የበለስ ቅጠል አድርገውታል። *[የዜና ቤተክርስቲያን ሙሉ ሀሳቡ ለማግኘት ይህን ሰንሰለት ይጫኑ፡- <u>"ዜና ቤተ ክርስቲያን የመስከረም 2007 ዕትም"</u> ወይም **ከዚህች መግለጫ መጨረሻው ገጽ ላይ ይመልከቱ።**]*

፫ኛ፡- ጉዳዩን ከአነሳሱ ጀምሮ በመከታተል ላይ ያለው ሕዝበ የእገዳው ሁኔታ እንዴት ከዚህ እንደደረሰና፤ ማስረጃውም ለአቡነ ማትያስ ተሰጥቶ፤ አቡነ ማትያስም "አዲስ አበባ እንደደረስኩ በአስቸኳይ ውሳኔው እንዲደርሳችሁ ይደረጋል" ብለው ማስረጃውን ሁሉ ይዘውት መሄዳቸውን በዲሲ፤ በቨርጅንያና በሜሪላንድ የሚኖረው ሕዝብ አይቷል ሰምቷል። ጉዳዩ ይህን ያህል ክብደት ያለው ሲሆን፤ በአገር ውስጥ ለሚኖረውና በውጭ ለሚኖረው ሕዝብ በ*<u>ዜና ቤተ ክርስቲያን</u>* ባቋራጭ እንዲንጸባርቅ ማድረጋቸው፤ ከላይ እስከ ታች ያለውን የቤተ ክርስቲያናችንን አመራር ከታላቅ ትዝብት ላይ ጥሎታል። <u>ክርስቶስ "የአሕዛብ አለቆች እንዲገዟቸው በላያቸውም እንዲሰለጥኑ ታውቃላችሁ"(ማቴ ፳፡፳፭) እንዳለው ይህች ጥንታዊት፤ ሐዋርያዊትና ታሪካዊት እያልን የምንናገርላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የአሕዛብ አለቆች ሰርስረው ገብተው በላያችን ላይ መሰልጠናቸውን እንድንረዳ አድርጎናል።</u>

አባ ፋኑኤልን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የዘረጋችውን ሐዋርያዊ ትውፊት ሰባብረው በመጣል፤ ብዙ ግፍና በደል የፈጸመውን ግለ ሰብ ደግፈው የቆሙት የከፋትና የጥፋት ሁሉ ሥርና ምንጭ በሆነው ፍቅረ ነዋይ በመነደፋቸው ነው።

የቤተ ክርስቲያናችን መውደቅ ቢያስጨንቃቸውማ ኖሮ፤ ምእመናኑ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የደረሰውን በደል በማስረጃ ሲያቀርቡላቸው፤ የቤተ ክርስቲያናችንን መርሆ በመከተል ምእመናኑን አረጋግተው፤ ተወጋቹንም መክረው ሁሉንም በሚያስተምር መንገድ ውዝግቡን መዝጋት ይችሉ ነበር። ነገር ግን፤ በግለ ሰቡ ላይ ጥፋት አየንባቸው ብለው በበቂ ማስረጃ ወቀሳና ክስ ያቀረቡትን ምእመናን በወታደር ሲያባርሩ፤ አልፈው ተርፈውም ስሜን አጥፍተዋል በማለት የሚሊዮን ብር ካሳ ለማግኘት በዳኛ ሲከስሱ፤ ከምእመናን አንዱ ትዳሬ በሳቸው ምክንያት ፈረሰ ብሎ ሲከስ፤ አባ ፋኑኤል አንድ ጊዜ "ጥርስ የሌለው አንበሳ ነኝ፤ ሌላ ጊዜ በኔ ሥር አይደለም። ገለልተኛ ነውና በአገሩ ሕግ ተፋለሙ" ባላሉ ነበር።

ይልቁንም ሁሉንም ያስገረመው፤ ተወጋቹ ግለ ሰብ በእርቅ እንዲስማሙ ተጠይቀው ባለመቀበላቸው በመመሪያችን መሰረት ከተወገዙ በኋላ፤ ምእመናኑም ጉዳዩን ከበቂ ማስረጃ ጋራ ለአቡነ ማትያስ አቅርበውት ነበር። መልሱን በአስቸኳይ እንደሚደርሳቸው በተገባላቸው ቃል መሠረት ከአቡነ ማትያስ ውሳኔ በመጠበቅ ላይ ሳሉ፤ አባ ፋኑኤል በደለኛውን ለመሸፈን የጻፉትን *በዜና ቤተ ክርስቲያን* ታትሞ እንዲሰራጭ የማድረግ ስልጣኑን እንዴት አገኙ? እንዴትስ ጥርስ ያለው አንበሳ ሊሆኑ ቻሉ? ለመሳሰሉት ብዙ ጥያቄዎች በራሳቸው ላይ የሚባርቁ ጥይቶችን በራሳቸው ላይ ደገኑ። በመጀመሪያ ግን "ሕገ ወጥ አመራርና ሕገ ቤተ ክርስቲያንን የሚቃረን ሥራ ሠሩ" ብለው በምእመናንኑ በቀሳውስቱ ላይ ያሸከሙንን የማጭበርበር ክስ ከላያችን ለማራገፍ እንሞክራለን።

## ፪ኛ. በሕገ ወጥ አመራር ሕገ ቤተ ክርስቲያንን የሚቃረን ሥራ አልሠራንም

ከኢትዮጵያ በመራቃችን፤ ለገንዘብ ክፍያ በሚያገለግለው መዝገብ ላይ ስማችን ባለመኖሩ፤ ወይም ቀድሞ ለሊቃውንቱ ይሰጥ የነበረውን የማዕረግ ስም ከቅስናችን በላይ ባለመደረባችን ካጠመቀችን ካስተማረችንና ክህነቱን ከሰጠችን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ገለልተኞች አይደለንም። ቤተ ክርስቲያናችን በአብነት ጉባዔዋ ነገረ መለኮቱንና ቀኖናውን አስተምራ ከሰጠችን ቅስና የበለጠ ስልጣን የለም። ስልጣነ ክህነት ከመስጠት በቀር፤ ከነገረ መለኮቱ ሳንርቅ ከቀኖናችን ዝንፍ ሳንል፤ አባ ፋኑኤል የሚሠሩትን በነገረ መለኮቱና በቀኖናው እየለካን ከማውገዝ የሚያግደን ነገር የለም። እኛም የልጅነት ዕድሜያችን በልጅነት ጨዋታ ሳንሰዋ እየታገልን ከዚህ የደረስነው፤ ቤተ ክርስቲያናችንም ያላትን ትጥቅ እያሸከመች ያሳደገችን ለዚህ አገልግሎት ነው። ስለዚህ እስከ አሁንም የተጓዝንበት፤ አሁን ያደረግነውና ወደፊትም የምናደርገው ሕገ ወጥ አይደለም። ሕገ ወጥና ገለልተኛ የሚያደርገንስ ከነገረ መለኮት ስንርቅ፤ ምሳሌነታችን በቂ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀርና አባ ፋኑኤልና መሰሎቻቸው የሚፈጽሙትን ስህተት ስንፈጽም ብቻ መሆኑን የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ሁሉ እንድትረዱልን አጥብቀን ማስገንዘብ እንወዳለን።

ጥንታዊት፤ ሐዋርያዊትና ታሪካዊት እያሉ እነ አባ ፋኑኤል የሚሰብኩላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን "አ ካህናት አንትሙ ውእቱ አዕይንተ እግዚአብሔር ብሩሃት። ተናጸሩ በበይናቲክሙ አሐዱ ምስለ ካልዑ። ሕቱ እምውስተ ህዝብክሙ በአበይኖ፤ ኢይቁም ወኢይህበር ምስሌክሙ በጸልዮ ኢዘማዊ ወኢቀታሊ ወዘያጣዑ ኢሰራቂ ወኢሐሳዊ ዘውእቶሙ ፫ቱ አክላብ እለ በአፍአ ይትኳነኑ" (ቅ አ ፰) ማለትም "እናንት ካህናት ሆይ የእግዚአብሔር ዓይኖች ናችሁና፤ በሕዝባችሁ መካከል እንከን እንዳይኖር በሚዛናዊ ፍርድ እርስ በርሳችሁ ተያዩ፤ ተመራመሩ፤ ተመዛዘኑ ተፈታተሹ። ዝሙተኛ ዋሾ ቀጣፊ ሌባ በመካከላችሁ እንዳይገኙ፤ በቅዳሴያችሁም እንዳይተባበሩ ምከሩ ገስጹ። ከቤተ ክርስቲያን ክልል ውጭ ያሉ ሰዎች በሚከሰሱበት አስነዋሪ ነገር የሚከሰስ የሚወቀስ ካለ ከመካከላችሁ እያወጋዛችሁ ለዩት።" የሚለውን መመሪያ እንደ ወተት እየጋተች፤ እንደ ማር እያላሰች ከዚህ ያደረሰችን፤ ይህን የመሳሰሉትን ፈታኞች ያለማቅማማት አንድንጋፈጥ ነው።

ከጥንታዊት፤ ከሐዋርያዊትና ከታሪካዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ክህነትን ከመቀበላችን በፊት፤ ልጅነት ሳያታልለን እስከ አንድምታው ጉባዔ ቤት ብዙ ዘመን ያሳለፍነው ሕጻናትን ለማጥመቅ ሙታንን ለመፍታትና፤ በቤተ ክርስቲያናችንም የሚያስነቅፍ እምነቱን የሚያስተች ነገር ሲፈጸም እያየን ታዝበንና አምተን ለመላፍ አይደለም። ይህ ካልሆነማ በየቀኑ በየዕለቱ "ዘወሀብከነ በመንፈስ ንኪድ ኩሎ ኃይሎ ለጸላኢ ከመ ንፍታህ ዘኢይትፈታህ" (ኪዳን) ማለትም "የማይፈታውን እንፈታ ዘንድ" እያልን የምንደግመው ባዶ ልፍለፋ መሆኑ ነው። ራሳችንንም ባይታወርና ምንደኛ (ቅጥረኛ) ማድርግም ነው። ይህም ደግሞ ትልቅ ኃጢአት በደልና ክህደት ነው።

በነዚህ ፳ ዓመታት፤ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን እንደተገነዘብነው፤ የቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርትና መርሆ ሳይማሩ ሰርስረው የገቡት ብዙዎቹ አጠንክረው የሚሰብኩት፤ ቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊት ሐዋርያዊት ክርስቶሳዊት መሆኗንና ስለ ጽጽስና ብፅዕና ቅድስና ብቻ ነው። በተጨማሪም ቀድሞ ባልነበረበት መልኩ በየቦታው የሚሰበከው ስለ ቁምስና ልዕልና ብቻ ነው። ይህም ይታወቅ ዘንድ መነኮስኩ የሚል ሁሉ የቁምስና ቅጽል ያለጠፈ የለም። ይህ ሁሉ ሽር ጉድና እሽቅድምድም የሚያሳየው ጸድቆ ሌላውን እንዲጸድቅ ለመርዳት ሳይሆን፤ ባዶ ክብር በመከናነብ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ተጠግተው፤ የሚጎርፈውን ክብርና የሚፈሰውን ገንዘብ ሳይወጡ ሳይወርዱ ያላንዳች ገደብና ጥርጣሬ ለመዝረፍ ነው። በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት ያሉትን ምእመናን ያንገሸገሻቸውን የኃጢአት ጎርፍ አባ ፋኑኤልን ሲያስተናገዱ ኖረው፤ አሁን ሕዝቡ ተንቀሳቅሶ ግፈኛ ቢጤያቸውን በማስወገድ የዘረጉትን የዘረፋ መረብ ሲበጣጥስባችው እንደ ነብር ተቆጥተው በመነሳት ቆሞስ አደርጌዋለሁ ማለታቸው ይህንኑ ደባ መፈጸማቸውን የሚያረጋግጥ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ዓለም የሚመስለውን ይወዳል” እንዳለው ፤ በሥርዓተ ገዳም ሳይታሹ፤ በሊቃውንቱ ሳይመከሩ በልብስ ስፌትና በሌሎችም ተግባራት ሲያድጉ ከመርካቶና ከፒያስ አካባቢ የወረሱትን ሁሉ ዓለማዊ ልምድ ሳያራግፉ እየተጠራሩ ወደ አመራር የገቡ ጳጳሳት መነኮሳትና ቀሳውስት፤ በአንደበታቸው ዘሙቱ ስረቁ ባይሉም፤ በግብራቸው የሚሰብኩት ከከተማ ይዘውት የገቡትን ዝሙቱንና ዘረፋውን ነው። በጥጋቸው የሚሰበስቧቸውም የሚመስሏቸውን ነው። ይህን መሳይ የዘቀጠ ባህርያቸውን የማይቀበሉትን የቤተ ክርስቲያኒቱን ሰዎች እያሳደዱ ናቸው።

የማህበረ ቅዱሳን ሰዎችም ከተከሰሱባቸው ነገሮች አንዱ፤ እነዚህን የመሳሰሉትን ሰዎች “አማሳኞች” በማለታቸው እንደሆነ ሲነገር ሰምተናል። በሰፊው ሲነገር የሰማነው እውነት ከሆነ፤ “የማህበረ ቅዱሳን ሰዎች የጳጳሳቱንና የቆሞሳቱን ስህተት የሚሰበስቡበት ዋና ዓላማ፤ ለታላቋ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸው ክብር ሲሉ ሳይሆን፤ ድርጅታችንን ደግፉልን፤ ባትደግፉን የሰበሰብንባችሁን ነውር ግልጽ በማድረግ እናጋልጣችኋልን። ከደገፋችሁን ግን እንሸፍናችኋለን። እንዲያውም ስለ ቅድስናችሁ ስለብፅዕናችሁ እየሰበክን ወደ ፓትርያርክነትና ወደ ታላላቅ መናብርትና ሥልጣናት እርከኖች እንገፋችኋለን“ እያሉ ለድርጅታቸው ድጋፍ ለማግኘት የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው” እየተባለ የሚነገርባቸውን እየተጸየፍን፤ ሳያዳሉና ሳይወግኑ ነውረኛውን ጳጳስ መንኩሴና ቄስ ለመገሰጽ በሚወስዱት ርምጃ እንድንተባበራቸው የቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ ያስገድደናል።

ነቢዩ ሆሴዕ “አማኙ የእምነቱን መምህር የሚሆነውን ይሆናል”(ሆሴዕ ፬፥፱)። ሲል የተናገረውን፤ መመሪያችን መሠረት በማድረግ፤ “እስመ ኖላዊ ለእመ ርኅቀ እም አመጻ ይስህቦሙ ለአርዳኢሁ ወያስተናሥእሙ ከመ ይኩኑ ተመሳልያነ በምግባራቲሁ ሠናያት በአማን” (፭፥፻፲፮) ብሏል። የሃይማኖቱ መምህር ከሥጋዊ ፍላጎት ቢርቅ ተከታዮቹን ወደ በጎ ሥነ ምግባር ይመራቸዋል። በሥጋዊ ፍላጎቱ ተሸንፎ ከወደቀ ግን አማኞችን ይዟቸው ይወድቃል። ከዚህ በኋላ ወደ ሰዶም ተግባር ከመሻገር በቀር የሚመልሰው ኃይል አይኖርም። በተጠመቅንባት እያስተማረች ባሳደገችን ጥንታዊት ሐዋርያዊትና ታሪካዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ይህ ተግባር ሲፈጸም ቆሞ ማየት ያሳምመናል። ይጎዳናል። በአምላካችንም ያስጠይቀናል።

እነ ቅዱስ አትናቴዎስ ከደረሱበት የቅድስናና የሞራል እርከን ላይ ባንደርስም፤ “ወንሕነሰ እለ ቅቡአን በጸጋ እግዚአብሔር በአማን ክርስቲያን ክርስቶሳውያን ወመሲሐውያን ወንኀሥዕ ንቅናዕ ወንቅረብ ከመ ንባዕ እምክብር ውስተ ብክብር”( አት ፴፯) እያሉ የተናገሩትን ባለመርሳት ወድቀን እንዳንታይ፤ ይልቁንም ከሞራል ልዕልናና ከቅድስና ለመድረስ ከራሳችን ሥጋዊ ባህርይና ከውጭም ከሚወረወርብን ፈታኝ ነገሮች ጋራ እየታገልን፤ ምእመናንን እንድናታግል እንጅ፤ እንደ እነ አባ ፋኑኤል ከወደቀው ጋራ በውድቀቱ እንድንተባበር ቤተ ክርስቲያናችን አላስተማረችንም።

አባ ፋኑኤልን የመሳሰሉ ሰብሮ ገቦች፤ ቀድሞ ለሊቃውንቱ ይሰጥ በነበሩት መልአከ ኪዳን; መልአከ ሰላምና በመሳሰሉት ቅጽሎች እንደ እነ ታደሰ ሲሳይ የመሳሰሉትን ቢጤዎቻቸውን እየሸፋፈኑ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን የሰገሰጓቸው፤ በሰሩት በደል ሲወገዙ ቤተ ክርስቲያናችን የዘረጋችውን መርሆ ተጠቅመው ወደ ንስሀ እንዲመጡ፤ ወይም ነጻነታቸውን አረጋግጠው ከውግዘት እንዲላቀቁ ከመምከር ይልቅ፤ ስለ ጳጳሳዊ የማይገሰስ ቃል (infallibility) እንዲሰብኩ ይገፋፏቸዋል። ይህን የሚያደርጉት ዋና ምክንያታቸው፤ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ክብር ቀናእያውያን ሆነው ሳይሆን፤ በለበሱትና በስም አጠራራቸው አክብረውና ፈርተው ከሚከተሏቸው

ምእመናን የሚጎርፈው ገንዘብና የሚፈሰው ክብር እንዳይጎድልባቸው ሲሉ ብቻ ነው።

እንኳን በነገረ መለኮትና በቀኖና ተደገፎ የተሰነዘረ ይህን የመሰለ ዕቀባ ወይም ግዘት ማንኛውም ሰው፤ የተሳሳተ ሰው ሲገጥመው "በሥላሴ በእግዚአብሔር ስም የምታደርገውን አቁም" ብሎ እንዲያግድ፤ እንዲያቆምና እንዲገታ ባህላችን ይፈቅዳል። ከምእመናኑ ጋራ በመቆም ለማስማማት ለማስታረቅ ሞክርን። ራሳቸው የቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይ እርቅ አሻፈረኝ አሉ። ከዚህ ሁሉ ሙከራ በኋላ፤ "በሕዝባችሁ መካከል እንከን እንዳይኖር በሚዛናዊ ፍርድ እርስ በርሳችሁ ተያዩ፤ ተመራመሩ፤ ተመዛዘኑ ተፈታተሹ። ዝሙተኛ፤ ዋሾ፤ ቀጣፊና ሌባ በቅዳሴያችሁ እንዳይተባበር ምከሩ ገስጹ። ከቤተ ክርስቲያን ክልል ውጭ ያሉ ሰዎች በሚከሰሱበት አስነዋሪ ነገር የሚከሰስ የሚወቀስ ካለ ከመካከላችሁ እያወጋዛችሁ ለዩ።" በሚለው መመሪያችን የቅድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይን ስንመዝናቸው፤ በጥንታዊት ሐዋርያዊትና ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያናችን መቀጠል የሚያስችላቸው ብቃት እንደሌላቸውና ከዚህ በታች የገለጽነው ስህተታቸው እንድናወግዛቸው አስገድዶናል።

## ፫ኛ. የቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይን እንድናወግዛቸው ያስገደደን

ካህኑ በዝሙትና በተለያዩ ነገሮች እየተወቀሱና እየተከሰሱ የቤተ ክርስቲያናችን ክብር የእምነታችን ቅድስና ሲጠፋ ነገሩ ያሳሰባቸው ምእመናን ተሰበሰቡ። የበደለኛውን ወላጅ እናታቸውንም ይዘን በእርቅ እንዲያልቅ ጣርን። ሰውየው ግን በፍቅረ ነዋይ የሰከሩ በመሆናቸው በሚሊዮን ብር ካሳ እፈልጋለሁና ወደ ሚያስከፍለኝ ዳኛ እሄዳለሁ ብለው፤ እርቅና ሰላም አሳፈረኝ አሉ። የገንዘብ እንጅ "ሰላም ለኩልክሙ" ብለው መቀደስ የማይችሉ እንደሆኑ ተረዳን።

ምእመናኑ በአካባቢው ላሉት ሁሉ ካህናትና ለኦርቶዶክስ ተከታይ ነኝ ብሎ ለሚያምነው ሁሉ በተለያዩ መስመሮች የዕርዳታ ጥሪያቸውን አስተጋቡ። "በዓለም ለመፍረድ አትበቁምን (፩ኛ ቆሮ ፮:፩__፯) የሚለውን ሐዋርያዊ መርሆ በመከተል ለማስታረቅ እኛ ከላይ ስማችን የገልጽን ቀሳውስት በነገሩ ገባንበት። በአካባቢው ያሉ ሁሉ ቆሞሳት ተመሳሳይ ችግር ያለባቸው ይመስል፤ ወይ በመካከል ገብተው ለማስታረቅ አልሞከሩም። ወይም መክረው የተነሳውን ውዝግብ ለማርገብ አላሰቡም። ያነጋገርናቸው ሁሉ "ግለሰቡ ከላይ እስከ ታች ካሉት ባለ ስልጣናት ጋራ የተሳሰረበት ሰንሰለት በቀላሉ የማይበጠስ ስለሆነ ተውት አትንኩት "ከማለታቸው በቀር፤ ታደሰ ያደርጋል እንጅ አያደርገውም የሚል አንድ ሰው እንኳ አላገኘንም። ራሳቸው ተከሳሹም "ማን ያልታማ አለ? በዚያውስ ላይ ሌላውን ሁሉ አልፋችሁ ለምን በኔ ብቻ መጣችሁ ከማለት በቀር አላደረኩም አላሉም። እርቁን አሻፈረኝ አሉ። ከዚህ ሁሉ ሂደት በኋላ በጉባዔ ወደተማርነው አዘነበልን።

ይህን ውሳኔ ስንወስንም ከራሳቸው ከአባ ፋኑኤል በመጀመር በአካባቢው አእማድ መስለው የሚታዩትን ሁሉ ምክር ጠይቀናል። ለአቡነ መልከ ጼዴቅ አካፈልናቸው "ከቅዱሳት መጻሕፍት ሳትርቁ መውሰድ የሚገባችሁን ርምጃ ውሰዱ" ብለውናል። የውስጡ ሲኖዶስ አባል ነኝ ብለው ኒዮርክ ያሉትን አቡነ ዘካርያስንም አማከረናል። እሳቸውም "በኔ ሥር አይደለም። የታያችሁን አድርጉ" በማላት ተመሳሳይ ሐሳብ ሰጥተውናል። በዚህም አልተወሰንም አቡነ ባስልዮስንና አቡነ መቃርዮስንም አማከርን። እነሱም ተመሳሳይ አሳብ ሰጡን። ደጋግመን እንደገለጽነው አባ ፋኑኤልንም አማከርን። "ጥርስ የሌለው አንበሳ ነኝ። ገለልተኛ ነው" የሚል መልስ ሰጡን። ከዚያ በኋላ ቤተ ክርስቲያናችን ባብነቱ ጉባዔዋ ወዳስተማረችን አዘነበልን። የክህነታችን ምንጭ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን መሠረት በማድረግ፤ የቅስናችንን አቅም ስልጣንና ችሎታ ፈተሽን። በተማርነው መሰረት ከቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ገለልተኛ የሚያደርገን አባ ፋኑኤልና የተወገዘው ግለ ሰብ የሚያደርጉት ስናደርግና፤ ከሚያደርጉትም ጋራ ስንተባበር ብቻ መሆኑን ተመለከትን። ከቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጋራ የሚያስተሳስረን ነገረ መለኮቷና ቀኖናዋ እንጅ፤ ገንዘብ ሹመትና ከንቱ የስም ድርርቦሽና ክብር እንዳልሆነም ተገነዘብን የወሰድነውን ርምጃ እንድንወስድ ከዚህ በታች የሰፈሩት መመሪያዎቻችን አስገደዱን።

*ሀ.* *"መሀርዎሙ ለእለ የሀውሩ ዘእንበለ አእምሮ ወለእለ ተምህሩ አጽንእዎሙ ወሚጥዎሙ ለስሁታን ወንግርዎሙ በኩሉ ጊዜ በእንተ 8ስህተቶሙ"*(፰; ፻፲፮) *ሕጉን ተምረው የረሱትን በማሳሰብ አጽናናቸው። በዝሁለ አዕምሮ ላይ ያሉትን አስተምሯቸው። የተሳሳቱትን እየገሰጻችሁ መልሷቸው የሚለውን መመሪያችንን ተመለከትን።*

ለ. “ኦ ብእሴ እግዚአብሔር ኍየይ እምዝንቱ ግብር ወዴግን ኀበ ኍሢሠ ጽድቅ ወርትዕ ወውስተ አሰረ ሃይማኖት ወተፋቅሮ ወታጋደል በእንተ ሃይማኖት ርትዕት” ወትረክብ ሕይወተ ዘለዓለም እንተ ተጸዋእካ ላቲ”(፩፡፮፲፩) ማለትም አንተ የእግዚአብሔር ሰው ነኝ የምትል ሆይ ከነገረ መለኮቱ ከቀኖናው ጋራ እየተጋጩ ካሉት ሽሽ። ከነገረ መለኮቱ ከቀኖናው ሳታፈነገጥ ፍትህ ርትእን በመፈለግ ተከተላት። የተጠራህላትን ዘላለማዊት ሕይወት ለማግኘት ስለቀናች ሃማኖት ሞራልና ሥነ ምግባር ተጋደል።” በሚለው መመሪያችን ሳይወሹ ሳይወላውሉ፤ ከነገረ መለኮቱ ዝንፍ ሳይሉ ከቀኖናው ጋራ ሳይጋጩ ከሚራመዱት በአካል፤ በገጠር በከተማ፤ በደብር በገዳም ካሉት እውነተኞች አባቶች ጋራና በመንፈስም በአጸደ ነፍስ ካሉት አባቶች ጋራ ባንዲት መርከብ ላይ እንዳለን ተሰማን።

ሐ. “ዘየአቅብ ትእዛዘ ኢየአምር ቃለ እኩየ። ወጊዜሁ ለፍትህ የአምር ልበ ጠቢብ”(መክ ፰፡፩) ማለትም በሕጉ የሚመራ ክፉ ነገር መናገር አያውቅም። አስተዋይ ልቡና ፍርድ የምትፈልግውን ቅጽበት ያውቃታል። የጎረጥ አይቶ አያልፋትም። የሚለውን አስታወስን።

መ. ቅዱስ ያዕቆብ “በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው” እንዳለው ከልጅነታችን ጀምሮ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት የተማርነው ነገረ መለኮቱ ሁሉ ይህንን የመሳሰሉ ነገሮች ሲገጥሙን መወሰን እንድንችልና የተማርነውንም አለመናገር፤ ስህተት ከሰራው ሰው ጋራ እኩል እንደሚያስፈርድብን ተገነዘብን።

ረ. መመሪያችንም ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚያስወግዱትን እየደረደረ መጥቶ “አው ዘየአምራ ለሕግ ወኢይገብራ ባቲ”(፮፡፪፻፳፬) በማለት አውቆ አለመስራት ከተደረደሩት ሁሉ የበደል ተግባራት አንዱ አድርጎ ወስዶታልና፤ በበደል መፈረጅን መንፈሳችን አልተቀበለውም ።

ሠ. ሰለስቱ ምእትም “ዛቲ ይእቲ ትእዛዝ ለሃይማኖት እንተ አቅደምነ ወጽሐፍነ ለእመ ገበርከ ዘንተ ትእዛዘ ወዐቀብከ ሃይማኖተ አማን ትከውን አንተ ረድኦ ለእግዚእነ”(ሃይ ፳፱፡፲፬) እንዳሉት፤ በብሉቱና በሀዲሳቱ ላይ መስርተው ስለ ቤክርስቲያናችን የጻፉ ያስተማሩ ሁሉ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት አበው ስህተት መስሎ በታየህ ነግር ከእውነት ፈቀቅ ሳትል ርምጃ ወስደህ የሚመጣብህን መስዋእትነት ከፈል እንጅ ሽሽ የሚል የለም። ከዚህ በታች በተገለጸው ስህተታቸው ላይ ተመርኩዘን ርምጃውን ወሰድን።

## ፬ኛ. እርምጃውን እንድንወስድ ያደረገን የግለሰቡ ስህተት

፩ኛ፡- ስለ ትዳር ቅድስና የሚያስተምር ካህን ይቅርና፤ ማንም አባል “መንፈሳችሁን ጠብቁ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል። መፋታትን እጠላለሁ ይላል እግዚአብሔር (ሚል ፪፡፲፩) የሚለውን መጠበቅ እንዳለበት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ታስተምራለች። የቀድሞው ቄስ ታደሰ ይህን ስህተት ፈጽመዋል። ፈጸሙ የተባሉትን ሌላውን ሁሉ ስህተት ትተን፤ ሚስታቸውን በመፍታታቸው ብቻ የሚገጥማቸውን ቅጣት መረመርን። “ወለእመ ተፈልጠ ቀሲስ አው ዲያቆን እምነ ብእሲቱ በምክንያተ ተልእኮቱ ለእግዚአብሔር ኢይደልዎ ተፈልጦ። ቄስ ወይም ዲያቆን በሌላ ምክንያት ይቅርና በአገልግሎት እንኳ ቢሆን ከሚስቱ መለየት የለበትም። ከሚለው ላይ አተኮርን። “ወእመሰ ኃደጋ ለብእሲቱ በዝንቱ ምክንያት ይትመተር። አገልግሎቱን ምክንያት አድርጎ ከሚስቱ ቢለይ እንኳ ካገልግሎቱ ይወገድ። ይህም ብቻ አይደለም። “ወከማሁ ለእመ አውጽኣ በምክንያተ ጽሙና ወምንኩስና“ (አ 6፡ 226) ከሚስቱ በመለየት የመነኮሰና የመነነ ቢኖር ምንኩስናውም ምናኔውም ውድቅ ነው።” የሚለውን ተመለከትን።

፪ኛ፡- “ወለእመ ተዳደቀ ሎቱ ፩ ወይቤ ከመ ውእቱ ኢይሴኒ ለኤጲስቆጶስ ለይህድር ግብሩ ሰለሰተ አውርኃ” በክህነቱ ላይ ጥያቄ ተነስቶ አንድ ሰው እንኳ ቢቃወመው፤ ጉዳዩ እስኪጣራ ድረስ ለሶስት ወራት ከክህነታዊው አገልግሎት ይወገድ።” የሚለውን ታደሰ መቀበል ፈቃደኛ አልሆኑም። እንዲያውም የሚሊዮን ዶላር ካሣ ለመቀበል ወደ ዳኛ ሄዱ። በድፍረትም ባገልግሎቱ ቀጠሉ። የገንዘብ እንጅ የክህነት ሰው አለመሆናቸውን በራሳቸው ፈረዱ። ይህን እየፈጸሙ “ሰላም ለኩልክሙ” ብለው መቀደስ እንደማይገባቸው ወስነን ርምጃ ወሰድን።

ቀጣዩ ርምጃ መሆን የነበረበት አባ ፋኑኤልም ሆኑ ሌላ፤ ይህን ግለ ሰብ የመሰለ ያለ አግባብ ውግዘት ተደረገብኝ ብሎ ሲቀርብለት፤ “ወእምዝ ይትከሰት በእንቲአሁ ግብሩ በህላዌ ዕድዉ ወበህላዌሁ ወለእመ ተአውቀ ላዕሌሁ ግብር ዘይከልእ በውስተ ቀኖናት እምተሠይሞቱ ይትከላእ”። ማለትም፡- ከሳሹ ባለበት ሆነ በሌለበት የተከሰሰበት ነገር ተዘርዝሮ ይነበባል። የሰራው ስህተት በቀረበው መረጃ ከተረጋገጠ ከተሾመበት ቦታ ይሻራል። ይልና በመቀጠል፡- “ወእመ አኮሰ ለይሰየም ወእድዉኒ ወኢያቀመ ላዕሌሁ ዘዘከሮ ለእመ ኮነ ህዝባዌ ለይተገሰጽ በከመ ይደሉ”(ፍ . አ 5፡ 99) ይላል።ይህም ማለት የቀረበበት ክስ በማስረጃ ያልተደገፈ ሀሰት ከሆነ፤ ክሱን ያነሳሱት ምእመናን ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደግሙ ይገሰጹ።” “እመሂ ኮነ ካህን ለይሰደድ እምቤተ ክርስቲያን” ከሳሹን አውጋዡ ካህን ከሆነ ከቤተ ክርስቲያን ይለይ ይላል። ይህን መመሪያ ቤተ ክርስቲያናችን ያስቀመጠችው፤ ምእመናን በሀሰት ተነሳስተው ንጹህ ሰው እንዳይጎዱ፤ ካህናትም በግፍ ተነሳስተው በንጹህ ሰው ላይ ውግዘት እንዳያደርጉ ነው። አባ ፋኑኤል ግን፤ ከመርካቶ ይዘውት በገቡት ሥጋዊ ፍላጎት የራሳቸውን ስሜት ለማርካት ሲሉ፤ በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት የተወገዘውን ግለ ሰብ በመደገፋቸው ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ!

የዚህች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን አካል ነን የምትል ሁሉ ! የቤተ ክርስቲያናችን ታሪካዊትነት፤ ጥንታዊነትና ሐዋርያዊትነት ያተረፈው ይህ በነ አባ ፋኑኤል ላይ የታየው ይሉኝታ፤ ሀፍረትና ገደብ የለሽ እራቁትነት መሆኑን ተገነዘቡ ! ተረዱ ! በጽጽስና ዙሪያ በተደረደሩት ቅጽሎች ራሳቸውን ሸፍነው፤ የቅዱስነት ቅጽል የተላበሰውን ሲኖዶስ ተገን አርገው የሚፈጽሙትን ደባ ቤተ ክርስቲያናችን የምትቀበለው አይደለም ። “ወደጇ ሆይ የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ? ብሎ ክርስቶስ የወሰደውን ርምጃና ቅዱስ ጳውሎስም “ከመካከላችሁ አስወጡት” (፩ኛ ቆሮ ፭፡፲፫) ብሎ የተናገረውን መመሪያ በመከተል ይህንን የመሳሰሉትን ርኩሳት ተግባራትየሚፈጽሙትን እንድናስወጣቸው ጥንታዊት ሐዋርያዊትና ታሪካዊት ቤተክርስቲያናችን አሰልጥናናለችና የወሰድነውን የመንፈስና የሞራል ሃላፊነት በታደሰ ብቻ የምንወሰን አይደለንም።

በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት የተከሰተው አሳፋሪና አሳዛኝ ስህተት፤ የብዙ ምእማናን መንፈስ አቁስሏል። ለብዙ ንዋየ ቅድሳት በከንቱ መባከን ምክንያት ሆኗል። ቤተ ክርስቲያኗ የተመሰረተችው ከዓለም ዙሪያ የመጡ ሰዎች በሰፈሩበት ቦታ በመሆኑና፤ 9 በዙሪያዋም ከተለያዩ ዓለማት እየመጡ የሚያርፉባቸው ሆቴሎች በመኖራቸው፤ በየሳምንቱ የሚደረገውን የተቃውሞ ድምጽ ከተለያዩ ዓለማት የሚያርፉትን ሰዎች ሁሉ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ላይ ነቀፋንና ትዝብትን እንዲሄዱ አድርጓቸዋል።አማሪካውያንን ባለስልጣናትንም እጅግ አሰልችቷቸዋል። ቅድስት ቤተ 8ስህተቶሙ መመሪያና ተቆርቋሪ የሌላት አድርጎ ለተመልካች ሁሉ አቅርቧታል። ይህ ሁኔታ ለዓመታት በመቀጠሉ ዓለም አቀፋዊነት ባህርይ ይዟል። አቡነ ማትያስም ጉዳዩን ይዘውት ወደ ኢትዮጵ በግባታቸው ብሔራዊነትንን ተላብሷል። አባ ፋኑዔል ይህንን ሁሉ ሸፍነው ዝም ማለታቸው እያሳዘነን ሳለ፤ እንዲያውም ይባስ ብለው፤ የተወገዘውን በደለኛ ግለሰብ ታይቶና ተደርጎ በማይታወቀ መንገድ ደግሰው ቆሞስ ሆኗል ብለው አወጁ። አቡነ ማትያስ እንደደገፉት፤ ሲኖዶሱም እንደተቀበለው አስመስለው በ*ዜና ቤተክርስቲያናችን* እንዲንጸባረቅ አደረጉ። ያንጸባረቁበትንም ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት ቅጽር ላይ መለጠፋቸው በደለኛውን ግለሰብ ሊያድኑ ሲሞክሩ ከጥንታዊት፤ ከሐዋርያዊትና ከታሪካዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጋራ በመጋጨት ራሳቸውን ወጉ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እያስተማረች ካሳደገችን ነገረ መለኮትና ቀኖና ዝንፍ ሳንል፤ ራሱን በራሱ በወጋ ግለሰብ ላይ ቤተ ክርስቲያናችን የምታዝዘውን ቅጣት ለተከታዮቿ ወገኖቻችን በማከታተል እናቀርባለን።

ይቆየን።

## ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ጠቅላይ ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ
እየታተመ በየወሩ ይወጣል።

ዋና አዘጋጅ፡- መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ
ም/አዘጋጅ፡- ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔር


# ርእሰ አንቀጽ

# የቤቶችና ሕንጻዎች አስተዳደርና ልማት ድርጅት አዲስ መሠረት ማኖሩም ሆነ፣ በጎ ላደረጉ መሸለሙ አግባብ ነው ነገር ግን...

የቤቶችና ሕንጻዎች አስተዳዳርና ልማት ድርጅት ባለፈው ነሐሴ ወር ፒያሳ በሚገኙ ዘውዱቱና መንበረ መንግሥት ሕንጻዎች መካከል ባለው ቦታ ሊያሠራቸው ላቀዳቸው መንታ ሕንጻዎች በቅዱስ ፓትርያርኩ መሠረት እንዲጣል ማድረጉ ድርጅቱ ከአስተዳደር ሥራው በተጨማሪ በተጨባጭ ወደ ልማት ተግባር መሸጋገሩን ፍንጭ የሚያሳይ ብሩህ ምልክት ነው።

በጠቅላይ ቤተ ክህነት በጀት በቸርችል ጐዳና እየተገነባ ያለው ባለዘጠኝ ፎቅ ዘመናዊ ሕንጻም የግንባታውን ሐሳብ ከማመንጨት ጀምሮ የግንባታው ሂደት እየተመራ ያለው በቤቶችና ሕንጻዎች አስተዳደርና ልማት ድርጅት በመሆኑ ለዚህ በጎ ሥራቸው የድርጅቱ አመራሮችና ሐሳብ አፍላቂዎች ሊመሰገኑ ይገባል። ከሁሉ በላይ እነዚህ የልማት እንቅስቃሴዎች መንግሥት የተወረሱ ቤቶችን ለቤተ ክርስቲያንዋ መመለስ ከጀመረበት ካለፉት ሃያ ዓመታት ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከናወኑ በመሆናቸው ድርጅቱ በተግባር ወደ አዲስ ምዕራፍ መሸጋገሩን የሚያረጋግጡ ናቸው። እነዚህ አዳዲስ የልማት ጅምሮችን ስናይ በድርጅቱ በኩል በቀጣይነት ሊተገበሩ የታቀዱ ግዙፍ ፕሮጀክቶች በሥራ ተተርጉመው ልናይ እንችላልን የሚል የተስፋ ጭላንጭል እንድናይ አድርጎናል።

የቤቶችና ሕንጻዎች አስተዳዳደና ልማት ድርጅት ጠንካራ ጐን ሆኖ ያየነው ሌላው ተግባር በቅርቡ በደርግ መንግሥት በግፍ ተወርሰው የነበሩ ሕንጻዎችን ለማስመለስ በተደረገው ጥረት የላቀ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ሦስት ግለሰቦች ዕውቅና የሰጠበት አካሄድ ነው። ጠንካራ ጐኑ ለሦስቱ ሰዎች ሽልማት መስጠቱ አይደለም። የቤቶችና ሕንጻዎች አስተዳደርና ልማት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ተስፋዬ ውብሸት በሽልማቱ ሥነ ሥርዓት ላይ እንዳሉት የሽልማቱ ዋና ዓላማ ተሸላሚዎቹ ባገኙት ሽልማት ይጠቀማሉ ማለት ሳይሆን ቤተ ክርስቲያናችን የእነዚህን አባቶች ውለታ ያልረሳች መሆኑን ለማመልከት ነው።

የዚህ ዓይነቱ አሠራር ተሸላሚዎችን ከማስደሰት ባለፈ አሁን በሥራ ያሉና ለወደፊቱ የሚመጡ አዳዲስ ሠራተኞችን በሥራቸው ይበልጥ እንዲተጉ ስለሚያግዛቸው ጥቅሙ መንታ ነው። በዚህ አጋጣሚ የእነዚህን ግንባር ቀደም አባቶችን ውለታ በማስታወስ ለሽልማት እንዲበቁና ስማቸው በክብር እንዲወሳ ያደረጉ የድርጅቱ አመራሮች አርቆ አስተዋይነታቸውን ያሳያል እንላለን።

ድርጅቱ ከላይ የተጠቀሱትን ጨምሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ አሠራሩን በማሻሻል ላይ ቢገኝም ሥር የሰደዱና እርምት የሚያሻቸው ደካማ ጐኖችም አሉት። ለአብነት ያህል ድርጅቱ ሕንጻዎችና ቤቶችን በማደስና በመንከባከብ በኩል እንደዚሁም በሥሩ ያሉ ለመኖሪያና ለንግድ የሚሆኑ ቤቶችን የሚያከራይበት አሠራር በዋናነት መጥቀስ ይቻላል። ድርጅቱ ከኪራይ ፍትሐዊነት ጋር በተያያዘ ያሉበትን ድክመቶች ለሌላ ጊዜ እናቆየውና ለአሁኑ በጨረፍታም ቢሆን የእድሳቱን ጉዳይ እናንሣ።

ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ በ1994ዓ/ም በመስከረም፣ በጥቅምትና በታኅሣሥ እትሞቹ ድርጅቱ በዚህ በኩል የነበረበትን በሙስና የታጠረ ችግር በማስረጃ በማስደገፍ ተከታታይ ምርመራዊ ዘገባዎችን ማቅረብዋ ይታወሳል። በእነዚህ ዘገባዎች መነሻነት በተደረገው ማጣራት በወቅቱ መሻሻሎች ታይተው የነበረ ቢሆንም አሁን ድረስ ከእድሳት ጋር የተያያዙ ችግሮች በተደጋጋሚ ሲስተዋሉ እናያለን።

ብዙዎች ሕንጻዎችና መኖሪያ ቤቶች (የንግድ ቤቶቹ በተከራዮቹ በየጊዜው ስለሚታደሱ ነው) ተገቢው እድሳትና እንክብካቤ ስለማይደረግላቸው እናት አባቱ እንደሞቱበት እጓለ ማውታ ሕጻን ተጐሳቁለውና ለተለያዩ ብልሽቶች ተዳርገው ይታያሉ። በአንዳንድ ሕንጻዎች ላይ ተደረጉ የሚባሉ "እድሳቶችም" ተከስተው የነበሩ ብልሽቶችን ያልፈቱ፣ የነበሩ ችግሮችን ያባባሱ፣ ለይስሙላ የተከናወኑ "መስና መስና የሚሸት" አሠራር የተስተዋለባቸው ነዋሪዎች ቅሬታቸውን ያሰሙባቸውና እያሰሙባቸው ያሉ ናቸው። የአንዳንድ ሕንጻዎች አሳንሱሮች /ሊፍቶች/ (ለምሳሌ የመንበረ መንግሥት) በብልሽት ምክንያት ከአገልግሎት ውጭ መሆናቸው ሳያንስ በተቆጣጣሪ አካል እጦት የቆሻሻ ማጠራቀሚያ በመሆናቸው በሕንጻዎቹ መወጣጫ ደረጃዎች ለመውጣትና ለመውረድ የፈለገ ሁሉ የግድ አፍንጫውን ሸፍኖ መሄድ አለበት።

ነዋሪዎችን አስተባብሮና አደራጅቶ የሕንጻዎችን ድህንነት ማስጠበቅ እየተቻለ በየሕንጻዎች የሚገኙ የጋራ መጠቀሚያ አካባቢዎች /መኪና መቆሚያ፣ ልብስ ማስጫ ወዘተ/ የቆሻሻ መጣያ እስከ ሚመስሉ ድረስ ይዞታቸው ተለውጦ ይታያል። የፍሳሽ ማስወገጃዎችና የዝናም ማውረጃ ቱቦዎች ጉዳይማ ባይነሳ ይሻላል። ሌላው ከቤቶቹ ደህንነት አንጻር ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ሆኖ ያገኘነው የቤት አመልካቾችን አፍ ለማስያዝ ወይም የባለሥልጣናትን ቁጣ ለማስታገስ በሚመስል መልኩ አንዱን ቤት ለሁለትና ለሦስት ሸንሽኖ በመስጠቱ በቤቶች ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት ነው። በዚህ የተነሣ የምግብ ማብሰያውን ወደ መኖሪያ ቤትነት፣ የእንግዳ ማረፊያውን /ሳሎንን/ ወደ ማዕድ ቤት የተለወጡበት በነበረው ቤት ውስጥ ከሕግ ውጭ በሆነ መንገድ ተጨማሪ ክፍሎች በመሥራት ሁኔታ እንዳለ ታዝበናል። በተለይ ሳሎንን ለምግብ ማብሰያነት መጠቀም የቤቱን መልክና ቅርጽ ከማበላሸት አልፎ የሕንጻውን ውሳጣዊ ይዘት ስለሚጐዳ የቤቱን የአገልግሎት ዕድሜ ሊያሳጥር እንደሚችል ከባለሙያዎች ጠይቀን ካገኘነው መረጃ ለማወቅ ችለናል።

እዚህ ላይ ከእድሳት ጋር በተያየዘ ለተከሰቱና ለሚከሰቱ ችግሮች ቤቶችን ከሚያስተዳድረው ድርጅት በተጨማሪ በጀት የሚፈቅደው አካልና ጉዳዩን በበላይነት ይመሩት የነበሩ የምህንድስና ባለሙያዎች ጭምር ኃላፊነት ያለባቸው ይመስለናል። በጥቅሉ ቤተ ክርስቲያናችን የዛሬ ብቻ ሳይሆኑ የነገ ተስፋዎቿ የሆኑትን ሕንጻዎች በአግባቡ ለመጠቀም ካስፈለገ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ እንዳሉት "ሕንጻዎችን አድሰንና ተንከባክበን" መያዝ አለብን። የሕንጻዎቹ የእድሳት ወጪን ለማቃለልና ዘለቄታዊ መፍትሔ ለማግኘት ከተፈለገ ደግሞ መንግሥት በሀገሪቱ የሚሠሩትን መንገዶች ለመጠገን ሲባል የመንገድ ልማት ፈንድ እንዳቋቋመ ሁሉ በሁሉም ተከራዮች ላይ ለእድሳት በሚል የተወሰነ መጠን ጨምሮ መያዝና ነዋሪዎች ቤቶቻቸውን በሥርዓት የሚይዙበት የተጠና ስልት ማበጀት ያስፈልጋል። ከዚህም በተጨማሪ ነዋሪዎች የተከራይቱን ቤት በሚገባ መያዛቸውንና አለመያዛቸውን በተወሰኑ ወራቶች እየሄዱ ቁጥጥር ማድረግ፣ ተከራዮች የተከራዩትን ቤት ለቀው ሲሄዱ ጥብቅ ቁጥጥር አድርጎ መረከብ፣ እስከ አሁን በአግባቡ እየተሠራበት ያልሆነ ነገር ግን ለቀጣይ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው እንላለን።◆

# በቬርጂኒያ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት አስተዳዳሪ ላይ በማይመለከታቸው አካላት ቀርቦ የነበረው ክስና ውሳኔ ውድቅ ሆነ

ከሕግ ቤተ ክርስቲያን ውጭ በሆነ አሠራር በሰሜን አሜሪካ ቨርጂኒያ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ በመልአከ ኪዳን ታደሰ ሲሳይ በማይመለከታቸው አካላት ተወስዶ የነበረው ከኃላፊነት የመሻር እርምጃ ውድቅ ሆኖ መልአከ ኪዳን ታደሰ ሲሳይ ወደ ቀድሞ ቦታቸውና ክብራቸው እንዲመለሱ መደረጉን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዋሽንግተን ዲሲ እና አካባቢው ሀገረ ስበከት ጽ/ቤት ለሚመለከታቸው ሁሉ በሚል ጁላይ 14 2004 ባሰራጨው ደብዳቤ አስታውቋል።

ብፁዕ አቡነ ፋኑኤል የሀገረ ስበከቱ ሊቀ ጳጳስ ፊርማና ማኅተም የተሰራጨው ይኸው ደብዳቤ በመሠረቱ አንድን ካህን ከሥልጣነ ክህነቱም ሆነ ከደረጃው የመሻር ብቸኛ መብት ያለው የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስና ቅዱስ ሲኖዶስ መሆኑ እየታወቀ የማይመለከታቸው አካላት የዚህ ዓይነት እርምጃ መውሰዳቸው ሕገ ወጥ አመራርና ሕገ ቤተ ክርስቲያንን የሚቃረን በመሆኑ ጥቂት ግለሰቦች



ተነሳሽነት መልአከ ኪዳን ታደሰ ሲሳይን ለመሻር የተወሰደው እርምጃ ሕጋዊነት የሌለው መሆኑ ጠቅሷል።◆

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን የዋሺንግተን ዲሲ እና
አካባቢው ሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት

THE ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO
CHURCH OFFICE OF THE DIOCESES OF
WASHINGTON D.C.
AND ITS SURROUNDING

July 14, 2014

To whom it may concern;

This letter is to make known that the sanction placed on Meleake Kidan Tadesse Sisay adminsitrator of Hamere Noh Kidanemehret Ethiopian Orthodox Tewahedo is not valid and against the canon of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church. The church is under the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church and Melake Kidan Tadesse Sisay is a member of the administrative committee of the diocese. We also would like to make it known that only an archbishop had the authority to bestow and also the power to revoke the honor of priesthood. Priests according to the canon of the church can not do the same.
Despite this standing regulation a few individuals without this mentioned power has passed a sanction against Meleake Kidan Tadesse Sisay therby disseminating false information to the faithful. These individuals are not recognized by the diocese and we would like it to be known that the so called "sanction" is against the Church's canon and absolutely with no merit.
I hereby would like to make it known that I as the Archbishop of Washington DC and California have the final authority to decide on such matters as delegated to me by the Holy Synod of The Ethiopian Orthodox Tewahedo church.

God bless us all

Abba Fanuel (Archbishop)

3010 Earl Pl. NE Washington D.C. 20018 tel. 571-214-3365